
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ቍጥር ፬

# የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ




፲ኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት መጽሔት

www.ethiopianorthodox.org

# ማረሚያ

| ግድፈት | እ ር ም | ገጽ | መሥመር |
|---|---|---|---|
| 1 ዕጨጌ የሚል | ዕጨጌ በሚል «ተብሎ ይነበብ» | 10 | 30 |
| 2 አልታገቱም | አልተገቱም » | 12 | 14 |
| 3 ሌላ እንጋገር | በሌላ እንጋገር » | 19 | 9 |
| 4 ተጠያቂ እንዳይሆኑ | ተጠያቂ እንጅ ጠያቂ እንዳይሆኑ | 23 | 14 |
| 5 ሲያገለግሉ የቆዩ ስለሆነ አንቀጽ | ይህ አንቀጽ ተብሎ ይነበብ | 24 | 29 |
| 6 የሚረዳ ጳጳሳት | የሚረዱ ጳጳሳት » | 25 | 20 |
| 7 $400.000 | $ 1.400000 » | 30 | 1 |
| 8 $599907 | $ 599207 » | 30 | 2 |
| 9 ተገብሮ መሥራት | ተባብሮ መሥራት » | 35 | 2 |
| 10 የኢትዮጵያ ድርሻ | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ | 37 | 26 |
| 11 ከዋናው መ/ ቤት ሠራተኞች መዋጮ $70360 | $ 3000 ተብሎ ይነበብ | 40 | 3 |
| 12 ከፓትርያርክ ጊሚን $3000 | $ 10350 » | 40 | 6 |
| 13 በድምር $138.850 | $ 128.850 » | 40 | 7 |
| 14 ለሕዝቡ መቶ | ለብዙ መቶ ዓመታት | 45 | 9 |

ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ ም

ይህ ሐዲስ ሕይወት የተባለው መጽሔት ለብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሦስተኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት መታሰቢያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ ዋና መምሪያ ተዘጋጀ ።


**አዘጋጅዎች**

መምህር ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ
ጌታቸው አበራ


www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org



ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋወሰን ኃይለ ሥላሴ
የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ

ጸጋት ረታና ቤተሰቢ የግል ቤተ መጻሕፍት

ገጽ

፩ ርእሰ አንቀጽ . . . . . . . . . ፲

፪ ሥርዓተ ክህነት . . . . . . . . . ፲፪

፫ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከመንበረ ፓትርያርክ የተሰጠ መግለጫ ፲፬

፬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና አስፈላጊነቷ . . . . ፲፰

፭ የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ የሕግ አቋም ከሚያጠናው ልዩ ኮሚቴ ለቅዱስነታቸው የቀረበ . . . . . ፳፫

፮ ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሕገ መንግሥታዊ አቋም የተሰጠ የማሻሻያ ሐሳብ ፳፬

፯ ነቅዕ ንፁሕ . . . . . . . . . ፳፯

፰ የዓመቱ ዋና ዋና መንፈሳዊ ነክ ዜናዎች . . . . ፴፪

፱ በድርቅ ምክንያት ለተጐዱት ወገኖች ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ርዳታ ፴፬

፲ ክቡር አቶ መኰንን ዘውዴ አዲሱን ሥራቸውን ጀመሩ . . ፴፯

፲፩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምግባረ ሠናይ ድርጅት . . ፵፩

፲፪ እስላሞች ስለአደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞ . . . ፵፬

www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# በታላቅ ትእግሥት የ ተገኘ መንፈሳዊ ነፃነት

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሥጋዊ ነፃነት በኩል የሦስት ሺህ ዘመናት ታሪክ እንዳላት በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ።

በዘመነ ብሉይ ከጽላተ ሕግ ጋር ፡ ከኢየሩሳሌም የመጡ ዕብራውያን ካህናት እንደ ነበሩ ቢነገርም ኢትዮጵያውያን የመጻሕፍተ ብሉያትን ምሥጢር ተምረው ፡ ሥርዓቱን ጠንቅቀው ካወቁ በኋላ የቤተ መቅደሱን ሥርዓት ራሳቸው በመንፈሳዊ ነፃነት ይመሩት ነበር ።

ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ ማለት ከሙታን ተለይቶ በመነሣት ባረገ በ፫ኛው ዓመት የጌታችን የምሥራች ዜና የሕይወት ብርሃን ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ እን ደገባችና የክርስትና ሃይማኖት እንደተመሠረተ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ። በሐ ዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፰ ቍጥር ፳፮—፵ የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ ሥምረት (ፈቃድ) የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያዊው መልእክተኛ እንደገባ የማያጠራ ጥር መንፈሳዊ መረጃ ነው ።

በአራተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ በቅዱስ አትናቴዎስ አንብሮተ ዕድ የተ ሾመ መንፈሳዊ አባት የመጀመሪያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ ከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማን አገኘች ። ፍሬምናጦስ ምንም እንኳ ተወላጅነቱ የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከሆኑት ሮማውያን ቢሆ ኑም በወጣትነቱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በአክሱም ቤተ መንግሥት ያደገ፤ የግዕዝን ቋንቋ ተማረ፤ የኢትዮጵያን ባሕል ያወቀና፣ ያጠናቀቀ በመሆኑ የውጭ ዜጋ በኢትዮጵያ ተሾመ ማለት አይቻልም፤ ቅዱስ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ፍሬምናጦስን የኢትዮ ጵያ ጳጳስ አድርጎ ሲሾመው እንደ ኢትዮጵያዊ ተመልክቶት ቆጥሮ እንጂ እንደውጭ ዜጋ እንዳልነበረ ፤ የጽጽስና አሰጣጡ ታሪክ ይመሰክራል ።

ፍሬምናጦስ «ስሙ ይመርሐ ኀበ ግብሩ» እንደተባለው አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ተብሎ የጵጵስናን ማዕረግ ተቀብሎ ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ የጐደለውን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አሟልቶ ፤ መጻሕፍተ ሐዲሳትን ከግሪክኛ ቋንቋ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተርጉሞ፤ የወንጌል ብርሃን በኢትዮጵያ እንዲያበራ አደረገ ፤ ስለ ሆነም በእውነት ከሣቴ ብርሃን ሆኖ ተገኘ ።

ከፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቀጥሎ ምን ሆነ ? የእስክንድርያ (የኮፕቲክ) ቤተ ክርስቲያን በልዩ ዘዴ ከዓረብ መነኰሳት ውስጥ የጵጵስና ማዕረግ እየሰጠች ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ከ፩ሺህ ፮፻ ዓመታት በላይ በመንፈሳዊ በኩል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይነትን ይዛ ኖረች ።

በየጊዜው በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት በሥጋዊ አስተዳደር በኩል ለማንም ሳት ደረከክ ነፃነትን ተጎናጽፋ የኖረች ኢትዮጵያ በመንፈሳዊ እርምጃ በኩል የቤተ ክርስቲያ ን መንፈሳዊ አስተዳደር የሚመራ «እጨጌ» የሚል መንፈሳዊ ሥያሜ የሚጠራ አባት ብ ዲመራ ቢያደርጉም ክህነትን የሚሰጥ፤በአባትነት ደረጃው ከሁሉ በላይ የሆነ፣ ነገሥ ታትን ቀብቶ የሚያነግሥ ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ ነበር ።

የመንፈሳዊ ነፃነትን ማጣት (መገፈፍ) ከዚህ የበለጠ ምን አለ ? «ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶቻችው መካከል ጳጳስ አይሹሙ » በማለት ጽፈዋል፤ይኸም ኢትዮጵያ በቀ ደም መንፈሳዊ ታሪኳ ያላትን ከፍተኛ ሥፍራ ለማጥፋት የተደረገ ሙከራ ነበር ። እው ነኛው ታሪክ ግን በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ከ፴፮ኛው እስከ ፹ በተመ



ለከተው ውስጥ በተለይም ፵፪ኛውና ፹፬ኛው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ኢትዮ ጵያውያን ራሳቸው ጳጳስ ከመካከላቸው መርጠው መሾም መቻላቸውን ያረጋግጣል ።

የግብፅ ዐረባውያን ጳጳሳት ቀስ በቀስ ገብተው ተጽዕኖ እስከ አደረጉበት ጊዜ ድረስ ከታላላቅ መንበረ ሊቀ ጵጵስናዎች ውስጥ ሰባተኛው መንበረ ክብር የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና ነበር፤ስምንተኛም ነው የሚሉ የታሪክ ጸሐፊዎች አሉ ።

የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በኋላ ዘመን ኦርቶዶክስነቱ የግሪክን ተየ ከተለው የግሩዚን ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ መንበረ ጵጵስና ጋር ተከታታዮች እን ደነበሩ ይናገራል ።

«እንተ ላዕለ ኩሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት» ተብላ የምትጠራ የሐዋርያት ጉባኤ የተባለች ጥንታዊቱ ቀጥተኛዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ታሪክ አልዘነጋውም ፤ ወደ ፊትም እንደያዘው ይኖራል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አበው ትዕግሥት ምን ይረቅ ? ምንኛስ ይጠልቅ ? መልካም ሥራ ሠርተው ፤ ሃይማኖትን ጠብቀው የኖሩ ሲሆን የጌታን ቃል በመከተል «እስመ ጽሩአን አግብርት ንሕነ» ምንም ምን ሥራን ያልሠራን ሎሌ ዎች ነን እያሉ በትሕትና አንገታቸውን አቀርቅረው ፤ የጵጵስናንም ክብር ሳይፈልጉ የግብ ፃውያን ጳጳሳት ተገዥዎች ሆነው ኖሩ ።

ትዕግሥት የባሕርዩ የሆነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እስከ መጨ ረሻው የታገሠ እርሱ ይድናል»ብሎ በአስተማረው መሠረት ኢትዮጵያውያን አበው ታግ ሠው ቆይተው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥረት በእግዚአብሔርም ፈቃድ በ፲፱፻፵ ዓ/ም ለኢትዮጵያ የራሷ የሆኑ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ ።

በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ (አቡነ ባስልዮስ) የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆኑ ።

የኢትዮጵያን ቋንቋና ባህል በማያውቅ በአንድ የአረብ ጳጳስ ብቻ ትመራና ትባ ረክ የነበረች ኢትዮጵያ ፲፰ ያህል መንበረ ጵጵስና እንዲኖራት እግዚአብሔር ፈቀደ ። ለክህነት ወደ አዲስ አበባ በመጓዝ የነበረው ችግር ሁሉ ተወግዶ «በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ታላቁ የፓትሪያርክነቱ መንፈሳዊ መብት ለኢትዮጵያ ተሰጠ ። የዚህ የድል አክሊል ባለዕድል ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆኑ ።

ብጹዕነታቸው የፓትሪያረክነቱን ሢመት ያገኙት ወደ ግብፅ ሔደው በካይሮ ከተማ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሲያርፉ፤ እግ ዚአብሔር በኢትዮጵያ መንበረ ፓትሪክና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ሲተካ፤ ኢት ዮጵያን ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ነፃነትን አጎናጸፋት ። ይኸውም በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ግንቦት አንድ ቀን በኢትዮጵያ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጸመው የቅዱስነታቸው የፓትሪ ያርክነት በዓለ ሲመት ነው ።

መንፈሳዊ ነፃነት የተለየው ሥጋዊ ነፃነት ነፍስ እንደ ተለየው ሰውነት መሆኑ የማያጠ ራጥር ነው ። ኢትዮጵያ ብዙዎች ዘመናትን በነፃነት የቆየች ሀገር መሆኗ በታሪክ ቢነ ገርላትም እንደዛሬው ሙሉ የሆነ መንፈሳዊ ነፃነት ስለአልነበራት በግማሽ ሕይወት ትኖር ነበር፤አሁን ግን የራሷን ልጅ መርጣ ፓትሪያርክ አድርጋ በመሾም መንፈሳዊ መብ ቷን ያስጠበቀችበት ጊዜ ስለሆነ የዛሬውን የቅዱስነታቸውን የ፫ኛ ዓመት በዓለ ሢመተ ፓትሪያርክና ስናከብር በታላቅ ትዕግሥት የተገኘ መንፈሳዊ ነፃነት ስለሆነ ፈጣሪያ ችንን ልናመሰግን ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ሥ ር ዓ ተ  ክ ህ ነ ት

ሥርዓተ ክህነት ከጥንት ጀምሮ ከአበው አባቶች የተመሠረተ በመሆኑ ሥርዓቱ ሳይፋለስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ መጥቷል አሁንም እንደጸና ይገኛል ።

የመጀመሪያው ፍጥረት አዳም ይህን ሥርዓተ ክህነት በመከተል የመጀመሪያው ጸሎቱ መሥዋዕት ለእግዚአብሕር ማቅረብ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለልጆቹ ማስተማር ነበር በኋላም በኖኅ የታቦት ምሳሌ ተገልጾ ይህን በመሰለ ዓይነት ሲፈጸም ከቆየ በኋላ ከአብርሃም ደረሰ እሱም በሥርዓተ ክህነት ሆ ኖ ልጁን ይስሐቅን ለመስዋዕት አቀረበ።ይህም የእግዚአብሔርን ፍቅር ያመለክታል።እግዚአብሔርም ስለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ለመግለጽ አብርሃምን«ዘርህን እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብትአበዛዋለሁ» የሚል ቃል ኪዳን ሰጥቶታል ይህም የሥርዓተ ክህነት ማዓረግና ክብር በሕገ ልቡና ከአበው ሲያያዝ መጥቶ ለያዕቆብ ልጅ በሌዊ የሥርዓቱ አመራር ተጀመረ።ያዕቆብና ልጆቹ በረሀብ ምክንያት ወደ ግብፅ ተሰደው ኑረው በሙሴ መሪነት ከግብፅ ከወጡ በኋላ ምንም እንኳ እምነታቸው ከእግዚአብሔር ያልራቀ ቢሆንም የግብፅ ሰዎች በአስለመዱት ልዩ ልዩየጣዖትአምኮ ተመርዘው ነበርና አልፎ አልፎ የማይጠቅም ልማድ ከመከተል አልታገቱም ነበር፤ግን እስራኤል ለአባታቸው ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የሰጠውን ቃል ኪዳን በተስፋ ሁነው በመጠባበቅ ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ለሙሴ አሥርቱ ቃላት የተጻፈባቸውን ሁለት ጽላቶች ሰጠው ሙሴም በጽላቱ የተጻፉትን ሕጎች ለሕዝቡ አነበበላቸው ። ለሁለቱም ጽላት መኖሪያ የሚሆን ታቦትና የታቦቱም መኖሪያ በሰ ማያዊት መቅደስ አምሳል ድንኳን እንዲሠራ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው የድንኳኑም ሥርዓት ተከናውኖ ካለቀ በኋላ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦት በዚያ ተቀመጠች፤ ለዚህም ሥርዓትና አገልግሎት በሥርዓተ ክህነት ከሌዊ ወገን ሌዋውያን ካህናትና መዘምራን ተመርጠው በአሮን መሪነት የክህነቱ ክብርና ማዕረግ እንዲሁም ሥርዓቱ ሁሉ ተጀመረ።ሕዝቡም በዚሁ ቃል ኪዳን ጸንተው እግዚአብሔር እኒህ ጽላቶች በአሉበት ታቦት አድሮ ሙሴን እያነጋገረው በታላቅ ኃይል ተአምራትንም እያሳየው ጠቅላላ የኦሪት ሕግ ተጽፎላቸው በዚህ ዓይነት የሕዝቡ ሃይማኖት ከተመሠረተ በኋላ ሙሴ ሞተ ። በሙሴ ምትክ ኢያሱ ተሾመ፤እሱም ወዲያውኑ ሕዝቡን እየመራ ዮርዳኖስን ተሻግሮ በከነአን የተስፋ ምድር ይኖሩ የነበሩትን በየክፍለ ሀገሩና በየነገዱ ተከፋፍለው በ፴፩ ነገሥታት ይመሩ የነበሩትን አሕዛብ ድል በማድረግ አባሮና አስወጥቶ ርስቱንና ከተማውን ሁሉ ለእስራኤል ልጆች አከፋፈለ፤የዚችም ታቦት ድንኳን ሴሎ በተባለው ቦታ ተተክሎ



ነበር በዚህን ጊዜ የክህነቱ ሥርዓት በአሮን ልጅ በአላዓዛር እየተመራ ኢያሱም ፴ ዘመን ካስተዳደራቸው በኋላ በመልካም ሽምግልና ዐረፈ ።

የእስራኤል ልጆች ከመካከላቸው በሚነሡት አንዳንድ መሳፍንት እየተመሩ ብዙ ዘመናትን አሳለፉ ዘመነ መሳፍንት አልፎ ዘመነ ካህናት ሲተካ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ዔሊ ፴ ዘመን አስተዳደራቸው ከሱም ቀጥሎ የተነሣው ነቢዩ ሳሙኤል ነበር ።እነሱም ሥርዓተ ክህነትን በመከተል ከአባቶቻቸው እየተላለፈ የመጣውን የፓትርያርክነት ክብር ጠብቀው ከኖሩ በኋላ ሕዝበ እስራኤል በንጉሥ መግዛትን ስለ መረጡ ነቢዩ ሳሙኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ሳኦልን ቀጥሎም ዳዊትን ቀብቶ አነገሠላቸው ። ዳዊትና ሳኦልም በተከታታይነት ፴ ፴ ዘመን ገዝተዋል ።

ከዳዊት ቀጥሎ ልጁ ሰሎሞን ነገሠ በነገሠ በ፬ኛው ዓመት የቤተ መቅደሱን ሥራ ጀመረ፤ ሥራውም እንደ ተፈጸመ በድንኳን ትኖር የነበረችውን ታቦት በዚያ አኖረ ፤ አባቱ ዳዊትም በ፳፬ቱ ሰዓተ መዓልትና ሰዓተ ሌሊት አራት አለቆች ያሏቸው አራት ሺህ መዘምራን በሥርዓተ ክህነት ሁነው ታቦተ ጽዮንን እንዲያገለግሉ አደረገ ።

ይህም ሥርዓት በ፬ት ሺህ አምስት መቶ ዐሥራ ስምንት ዓመተ ዓለም በንግሥት ማክዳና በንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በልጁ በምኒልክ አማካይነት በኢትዮጵያ ተጀመረ ሥርዓቱን ይመራው የነበር ሊቀ ካህናት አዛርያስ ቢሆንም በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕገ ኦሪትንና ሥርዓተ ክህነትን ተምረዋል ። ይህም ሥነ ሥርዓት ለልጅ ልጅ እየተላለፈ እስከ ክርስቶስ ልደት ደረሰ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘመነ ሐዲስ የመጀመሪያው ሊቀ ካህናትና ፓትሪያርክ ተባለ ።

መ/ መልአኩ ፈለቀ



www.ethiopianorthodox.org

# ስለቤተ ክህነት አስተዳደር ከመንበረ ፓትርያርክ የተሰጠ መግለጫ

ኢትዮጵያ በቤተ ክርስቲያኗ ፣ ቤተ ክርስቲያኗም በኢትዮጵያ፣መታወቅ ከጀመሩ ብዙ ዘመናት አልፈዋል ። ይህም ሊሆን የቻለው ሕዝቡ ሃይማኖቱን ፣ የኢትዮጵያዊነቱ ክብር አርማ አድርጎ ለአንዲት ሀገር ፣ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ተባብሮ በመሥራትና ተዋሕዶውን በማጽናቱ እንደሆነ ፣ አያሌ ታሪክ ጸሐፊዎች መዝግበውት ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፎ የዛሬዪቱን ኢትዮጵያ ነዋሪዎችም በጠቅላላ ለታሪኩ ባለቤትነት አብቅቶናል ። እንዲያውም የዓለምን ታሪክ ከመረመሩ ሊቃውንት መካከል «የኢትዮጵያ ታሪክ የነገሥታቷና የአብያተ ክርስቲያናቷ ታሪክ ነው» ብለው በግልጽ የጻፉ በቁጥር የበዙ ናቸው ። ይህም አነጋገር የኢትዮጵያ ታሪክ በችሮታ የተገኘ አጋጣሚ ስጦታ አይደለም ። በረጋና በንጹሕ መንፈስ ለሚመሰክር ሁሉ ፣ እስካሁን ድረስ ነገሥታቱ ለቤተ ክርስቲያን እንደተሰጡ ፣ ነገሥታትና ምእመናኑ የሃይማኖታቸውና የሀገራቸው ጠባቂዎች መሆናቸውን አምነው ለአንዲት ሃይማኖት ፣ ለአንዲት ሀገርና ለአንዲት መንግሥት ጋሻና መከታ በመሆን ጠረፋቸውን አስከብረው ፣ ጠላታቸውን አሳፍረው ፣ ፍቅርና ሰላም በሰፈነበት አንድነት መኖራቸው የማይሰወር እውነት ሆኖ ስለተገኘ ነው ።

ኢትዮጵያ ከሌሎቹ የአፍሪቃ አህጉር ተለይታ በነፃነት የኖረችበትንም ምሥጢር ስንመረምር ፣ ከዚሁ ታሪክ አድማስ ልናልፍ አንችልም ። በአፍሪቃ ምሥራቅ ተፈጥሮ ስላስቀመጣት አይደለም ። በተራሮች ወንዞችና ሸለቆች ተውባ፣ዓመቱን በሙሉ የሕይወት ነፋስ ስለሚነፍስባትም ብቻ አይደለም ። እርግጥ ነው እነዚህ ሁሉ ከፈጣሪ በጸጋ የታደለቻቸው በረከቶች ናቸው ። ለዚያ የረጅም ጊዜ የነፃነት ታሪክ ያበቃት ግን ሌላ ነው ። ይኸውም ሃይማኖት ነው ።

«ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ ፣ እግዚአብሔርም ኢትዮጵያን ሳይጠብቅ የኖረበት ዘመን የለም» ተብሎ ተደጋግሞ ተጽፏል ። የብሉይ ኪዳን ትንቢት፣የሐዲስ ኪዳን ትምህርት፣ተፈጽመውላታል ። ይህ ሕዝቦቿ በነገሥታቷ መከታነት ከቤተ ክርስቲያናቸው የወረሱት ጠንካራ የሥነ ምግባር ቅርስ ስለነበረ ከዕለት ጥቅማቸው ፣ ለዘላቂ ሃይማኖታቸው ፣ ከራሳቸው ለሀገራቸው ፣ ከዘመዶቻቸው ለሰብአ ሀገራቸው ፣ በማሰብ ሀገራቸውን ከአህጉሩ ለይተው «ነፃይቱ ኢትዮጵያ»በማሰኘት ለሌሎች አብነት እንድትሆን አድርገው ለኛ አውርሰዋል ። «በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ እኩል ነው » እንደሚባለው ካልሆነ በቀር ፣ ለማንም ሀገር በአንድነትና በፍቅር ከተገኘው ሰላማዊ ነፃነት የበለጠ ፣ የብልጽግናና የዘላቂ ኑሮ ዋስትና ሊገኝ አይችልም ። ኢትዮጵያን በአለችበት ክፍለ ሀገር የሚያኮራ ባህል ግምጃ ቤት ፣ የኪነ ጥበባት ቅርሳ ቅርስ መደብር ፣ የሥነ ጽሑፍ ገበያ ሆና ዜጎቿን ጠቢባን ፣ ነገሥታቷን ኃያላን ፣ የሃይማኖት መሪዎቿን ቅዱሳን አሰኘኝታ ዓለምን ስታስደንቅ የኖረችው በዚህ ሰላም በሰፈነበት ፣ የማያወላውል እምነት መሠረቱን በጣለበት ፣ የሚያኰራ ነፃነት መሆኑ ፣ ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን የተሠወረ መስሎ መታየት የለበትም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ሁሉ ባለውለታ ናት ። ምንም እንኳን ክርስትና ወደሀገራችን የገባው በአንደኛው መቶ ዘመን ቢሆን ፣ ቅዱሳን ነገሥታት አብርሃና አጽብሐ በይፋ በአጸደቷት መንግሥታዊት ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ከዐራተኛው መቶ ዘመን ጀምረው የተውልን ይህ የአንድነትና የወንድማማችነት ክርስቲያናዊ ጸጋ ታሪካቸውን የማይሞት ፣ ሕዝቡን በተራ አስተሳሰብ የማይገመት ፣ አድርጎት ስለሚኖር ሀገራቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሲኰሩበት ይኖራሉ ።

የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔርና እነዚህን ከመሳሰሉ ነገሥታት በጸጋ ያገኘችውን በረከት ጠብቃ የመንፈሳዊና የሥጋዊ ጥበብ መሪ በመሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት በማጽናት በዳዊትና በጋሻ ሕዝቡን ለአንዲት ሀገር ደኅንነት በማሠለፍ በአንዲት ሀገር ተፋቅረው እንዲኖሩ ስላደረገች ሀገሪቱ ሀገረ እግዚአብሔር ፣ ሕዝበ እግዚአብሔር ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሥዩመ እግዚአብሔር ፣ እየተባሉ ሲጠሩ ኑረዋል ።

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ምእመናን በነገሥታቱ አበረታችነት የሠሯቸው የታሪክ ኪነ ጥበባት በሙሉ በሃይማኖታዊ ተመሥጦ በረድኤተ እግዚአብሔር ተጀምረው በረድኤተ እግዚአብሔር የተፈጸሙ ትንግርቶች ስለሆኑ ፣ ዛሬም ኢትዮጵያን የዓለም ጠበብትና ሊቃውንት ተመራማሪዎች የማትጠገብና የማትሰለች የትምህርት ሸንጎ እንድትሆን አድለዋታል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትም ጥንትም ሆነ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታዎች ናቸው ። ከጥንቱ ሥነ ጥበብ ወደ አዲሱ የትምህርትና ሥነ ጥበብ መሸጋገሪያ ድልድይ መሆናቸውን የማያውቅ ይኖር አይመስለንም ። ሌላው ቢቀር በቤተክርስቲያን ትምህርት ቤት ፊደል የቆጠረው የዘመናችን ወጣት ቁጥር እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ ራሱ የተማረው ያውቀዋል ። የእውቀት መሥፈሪያው ፊደል መቁጠር ፣ ማንበብና መጻፍ ነው ባይባልም ፣ ሀገራችን በፊደል ሠራዊት ለምታደርገው አጣዳፊ ዘመቻ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፊታውራሪና ደጀን መሆኗ መዘንጋት የለበትም ። ቤተ ክርስቲያን በጥንታዊና ዘመናዊ ደረጃ ለይታ ከምትሰጠው ትምህርታዊ አገልግሎት ሌላ ፣ ቦታ ጊዜና ሰው ሳይለዩ ካህናት በንባብ ትምህርት የሚሰጡት የጸጋ ተራዶኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ መንገድ ጠራጊ መሆኑን ታሪክ እየዋለ እያደረ ሊመሰክር ይችላል ። የእነዚህ በራሳቸው ወዝና በሕዝብ ርዳታ ነፃ አገልግሎታቸውን እያበረከቱ የሚኖሩ ካሕናት ውለታቸው የሚረሳ አይደለም ።

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ በመንግሥቱ በቤተ ክርስቲያኑ የጠበቀ ታሪካዊ ግንኙነት ምክንያት ይኸ የመንግሥት ነው ፣ ይኸኛው የቤተ ክርስቲያን ነው ፣ ሳይባል ሥራቸው የጋራ ሆኖ መንግሥቱ የቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያንም የመንግሥቱን ሥራ ጭምር እየተረዳዱ ለአንዲት ሀገርና ለአንድሕዝብሲያበረክቱ መኖራቸው ግልጽ ነው ።

ለዚህም ግልጽ ማስረጃ ቢፈለግ በዘመናችን ያሉት የሃይማኖት ጠባቂ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሀገራቸው ጳጳሳት ተባርከው የክህነት አገልግሎታቸውን በየአሉበት እንዲፈጽሙ ለማድረግ በትዕግሥት ያደረጉትን ከፍተኛ ድካም ማንም ያውቀዋል ። ኢትዮጵያውያን ፍጹም ነፃ በሆነ ኢትዮጵያዊ መንበረ ፓትርያርክ ሥር መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ከማድረግ የበለጠ የሥራ ፍሬ ምንጊዜም አይጠበቅም ።

መቸም ቤተ ክርስቲያናችን እስካሁን ድረስ የኖረችው በዚህ ዓይነት መንፈስና አገልግሎት ብቻ ባይሆንም ፣ በአላት አቅምና ችሎታ ለሀገርም ሆነ ለወገን የነፈገችው አገልግሎት የለም ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከአለችበት ዘመን ወደ ኋላ ለማፈግፈግ አትችልም ። የብሉይኪዳንምመለኮታዊትንቢትሲፈጸም የዚህ ጸጋ ተካፋይ መሆን ስለሚገባትከአባቶቿ ከሐዋርያት ትምህርትና መመሪያ ልትገለል አልቻለችም ። ቤተ ክርስቲያናችን ኦርቶዶክሳዊት እንደመሆንዋ የቆየ ልማድና ሥርዓት ስላላት አንዳንዶች እንደሚያስቡት ማንኛውንም ርምጃ እንደ ዋዛ ልንመለከት አይገባም ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መንፈስ እንድትሠለፍና የወጣቶችም ልብ ወደ አባቶች እንዲመለስ በጸሎት ፈጣሪን እየለመን ቤተ ክርስቲያናችን በዘመናዊ አቅድ እንድትመራ መጩውም ትውልድ በከፍተኛ የጋለ

www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተካፋይ እንዲሆን በማሰብና ፤ እንደዚሁም የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገራችን ያላትን ክብ ርና ስፍራ ጠብቃ እንድትገኝ ከዚህ በሚቀጥሉት አርእስቶች ላይ መሻሻል እንዲደረግ ባቸው መምሪያ ይሰጣል ።

፩ ፤ ኢትዮጵያ በትምህርት በኩል በየቤተ ክርስቲያናቱና በየመንደሩ ሕፃናትን ስታ ስተምር መኖርዋ አዲስ ነገር ሳይሆን ፤ ዛሬም በትምህርት በኩል ለመንግሥት ከፍተኛ ርዳታ ትሰጣለች ፤ ይህ አገልግሎትዋ ሳይቋረጥ ትምህርት በየገጠሩ እንዲስፋፋ፤ የትምህርቱም አሰጣጥ እንዲሻሻል፤ ከመንግሥቱም ሆነ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በይበልጥ በመተባበር ማንበብና መጻፍ ለማይችሉት ወገኖቻችን ርዳታው የሚደርስበትን እያስጠናች እንድትሠራ ይደረጋል ።

፪ ፤ የቤተ ክርስቲያን ዋናው ዓላማ በገጠር፤በከተማ፤ በጠረፍ፤ ወንጌልን በማስተማር ፤ የክርስትናን እምነት ማዳረስ ስለሆነ ፤ በዚህ ሁኔታ ከዚህ በፊት ከተወሰደው እር ምጃ በተሻሻለ እቅድ ስብከትን ከአካባቢው ኑሮ ጋር በማስተባበር መስበክና ማስተማር ቅድሚያ ተግባር ስለሚሆን ከመቼውም ይልቅ ስብከት እንዲስፋፋ በብርቱ ይጣርበታል ።

፫ ፤ በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙት ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩበት ሁኔታ እየተጠና ፤ የቤተ ክህነት አስተዳደር ዘመኑን የተከተለ ሆኖ እንዲገኝ ፤ የሠራተኛ መብት እንዲጠበቅና አስፈላጊው ሁሉ እንዲሻሻል ጥረት ይደረጋል ።

፬ ፤ የቤተ ክርስቲያንን ተግባርና ዓላማ በሚገባ ለማስፈጸም ገንዘብ ያስፈልጋል ፤ ጥንትም ሆነ አሁን የቤተ ክርስቲያን ሀብትዋ ሕዝቧ ነው ። እስካሁን ድረስ ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ፤ ርስት ፤ መለገሱ አልቀረም ። የሕዝቡን በጎ ፈቃድና የማይቆጠብ ርዳታውን በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋልና ሀብትዋን በሚ ገባ ለመቈጣጠር የገቢ ምንጮችዋ ተጠንተው ያሉት እንዲጠነከሩ ሌላም ቢኖር እያስጠናች ለመከታተል ከምእመናንዋ ጋር ትተባበራለች ።

፭ ፤ የዓለም መርማሪዎች አተኩረው የሚመለከቱት የኢትዮጵያን ጥንታዊ ቅርሶች ስለ ሆኑ እነዚህ ቅርሶች የቤተ ክርስቲያንና የሀገራችንም የባህል ቅርሶች ሆነው ስለም ናገኛቸው እነዚሁ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች ባላቸው መልክ ተጠብቀው ለጥናት ምቹ ሆነው እንዲኖሩ ቤተ ክርስቲያን ጥረት ታደርጋለች ።

፮ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን የቆየ ግን ኙነት በማጠንከር አሁንም ቢሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ግዳጅ በመከ ተል ለጠቅላላው የዓለም ክርስቲያናት ግንኙነት በኅብረት ትሠራለች ።

፯ ፤ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን እንደመሆንዋ ንጉሠ ነገሥቷም የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ እንድትተዳደር የደከሙላት ስለሆነ፣ መንግሥት በሚያደርገው የሕዝቡ የኑሮ መሻሻል ጥረት ደጋፊ በመሆን የልማት ኮሚሽንዋን በማጠንከር ከውስጥም ሆነ ከውጪ በሚገኘው ርዳታ የሕዝብ ኑሮ መሻሻያ በ ፂ ሆንበት ልማት ደጋፊና አነቃቂ እንድትሆን በይበልጥ ይሠራበታል ።

፰ ፤ ለሀገር ከሚፈለጉት ልዩ ልዩ ልማቶች ፤ ዛፍ አንደኛው ክፍል መሆኑን የማያውቅ የለም ። የዛፎች አለመኖር ለድርቅ ምክንያት ይሆናል ። በኢትዮጵያ በብዛት ዳብ ረውና ተጠብቀው የሚገኙ ዛፎች በገዳማትና በአድባራት አካባቢ ነው ። ይህ የቆ የው የዛፍ ልማት በበለጠ እንዲዳብር ማድረግ ለቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ሥራ



ሲሆን ፤ ሀገርን በልማት ከሚያበለጽጉት አንደኛውን ክፍል በበለጠ አጥብቃ እንድ ትከታተል ይደረጋል ።

፱ ፤ የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት የዕውቀት ምንጭ የጥበብ መገኛ በጠቅላላው ለዓ ለም ሰላምና ኅብረት እንዲገኝ የሚጸለይባቸው ቦታዎች ስለሆኑ ክብራቸው በይበ ልጥ የሚጠበቅበትን ምርምርና ጥናት ታደርጋለች ።

፲ ፤ የቅዱሳት መካናትን የጠበል ቦታዎች ለሕዝቡ ምቾትን እንዲሰጡና የቦታው ቅድ ስናም እንዲጠበቅ ይሆናል ።

፲፩ ፤ የጥንት መጻሕፍት ብዙዎች በግዕዝ ተጽፈው በየቦታው ተቀምጠው ስለሚገኙ እያ ስተረጐመችለሕዝቡ እንዲዳረስ ለማድረግ የግዕዝ ቋንቋችንም ደረጃ ውን ሳይለቅ እየተሻሻለ በሥራ ላይ የሚውልበትን ታስጠናለች ።

፲፪ ፤ በቤተ ክርስቲያን በኩል ስለሚገኘው የመሬት ይዞታ በያለበት የሚተቸው ትችት ቦታና ተቀባይ እንዲኖረው የቤተ ክርስቲያንን የመሬት ይዞታ ሁኔታ የሚገልጽና ይዞታውም ምን ያህል እንደሆነ ሙሉ ጥናት ተደርጎ ይገለጣል ።

፲፫ ፤ ከዚህ በፊት ስለሰበካ ጉባኤ የወጣው ደንብ በብዙ ቦታዎች ተቀባይነት በማግ ኘቱ ደስ ብሎናል ። ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች አሁንም በትክክል ያልተረዱት ስለሆነ ፤ ጥቅሙና ጉዳቱ የሥራውም አፈጻጸም በተብራራ ሁኔታ እየተዘጋጀ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ እንዲውል ብርቱ ጥረት ይደረጋል ።

፲፬ ፤ የካህናት ሕይወት ዘመኑ በሚፈቅደው መልክ እንዲጠበቅ የመጀመሪያ ጥረታ ችን ይሆናል ። ከዚህም በላይ እቅዳችን ሁሉ ይከናወናል ብለን የምናምነው ታሪክ እንደሚመሰክረው በካህናቱ ኅብረት ስለሆነ ፤ የመሻሻል ድልድይ እንዲሆኑና ያለንን አቅምና አቅዋም እያመዛዘንን እንድናደርገው አደራ ጭምር እናሳስባለን ።

፲፭ ፤ ስለ ቤተክርስቲያን አስተዳደር የዋናው ሥራ አስኪያጅ ኃላፊነትና ተግባር በሕግ ክፍል በቍጥር ፫፻፷፬/ ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በወጣው መሠረት ፤ የቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ እነዚህን ሁሉ በሙሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ በጥናት ፤ በምርምርናበሐ ሳብ የሚያማክር የቤተ ክህነት አስተዳደር አሥራ ሁለት አባሎች ያሉት ጉባኤ ከካህናትና ከምእመናን ተመርጠዋል ።

፲፮ ፤ ከላይ የተጠቀሰው ጉባኤ «የቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ» እየተባለ ይጠራል ።

ለዚሁም ጉባኤ ኃላፊነትና አሠራር ራሱን የቻለ መምሪያ ይሰጠዋል ።
ይህ የመሻሻል እቅድ ከሥራ ላይ ውሎ እንድናይ የእግዚአብሔር ፈቃዱ እንዲ ሆን እንለምነዋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና አስፈላጊነቷ

## መግቢያ ፤

ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት በመባል ለብዙ ዘመናት የቆየች ሀገር ናት ። አባባሉ በእርግጥ ተገቢ ነው ። ምክንያቱም በእዚህ ክፍለ ዓለም በተለይም በቀይ ባሕርና በሜዲትራንያን ባሕር ዳርቻ ባሉት አገሮች የክርስትና ፀዳል ከመጀመሪያው የክርስትና ምዕት አንሥቶ ተራ በተራ የተፈነጠቀ ሲሆን ከ፯ኛው ምዕት ዓመት በኋላ ቀስ በቀስ ብርሃኑ እየከሰመሲሄድ በኢትዮጵያ ላይ ብርሃኑ ደምቆ እስካሁን አለ ። በሌሎች አገሮች በተለይ በሰሜን አፍሪካ ክርስትና ሥፍራውን የለቀቀበትን ምክንያትመመራመርትተንለምን ክርስትና በኢትዮጵያ ኖረ?በሚል ቃለ መጠይቅ ነገሩን መመልከት ይበቃል ። ለዚህም ነገሩን ከሥሩ ማየት ስለሚገባን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠባይና አስፈላጊነቷን በዝርዝር እንመልከት ።

## የቤተ ክርስቲያን ጠባይ

ክርስትና በገሃድ የተሰበከው በ፬ኛው ምዕት ሲሆን፤የክርስትና በኢትዮጵያ መሰበክ ከሌሎች አገሮች ፍጹም የተለየ ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስትናን ፈልጎ አመጣ እንጂ ክርስትና ኢትዮጵያን ፈልጎ አልመጣም ። ድርጊቱ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ነው ። እስከ ፬ኛው ምዕት ድረስ የክርስትና ታሪክ ከጭንቀትና ከመከራ ጋራ የተያያዘ ነው ። ክርስትናን ለማስፋፋት በሆነው ሙከራ ብዙ ደም አፋሷል፤ የብዙዎችን ሰባክያን ሕይወት አጥፍቷል ። ፬ኛው ላይ ስንደርስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስትና በሀገሪቱ እንዲሰበክ መምህራንን ይጠይቃል ። የጠየቀውን ም ያገኛል ። ይህ እንግዲህ አዲስ የቤተ ክርስቲያን ምዕራፍ ነው ።

በዚህ አኳኋን ክርስትና በኢትዮጵያ ከተጀመረበት አንሥቶ የሀገሩ ዋና ሃይማኖት ነው ። ምንግዜም ጥገኛ ሆኖ አያውቅም፤ወደፊትም አይሆንም ። ንጉሡ ነገሥቱ ክርስትናን በገሃድ ሃይማኖት እንዲሆን ያወጀው የድንጋይ ጽሑፎች ላይ እንደ ተቀረጸው፤ዔዛና ሲሆን በመጻሕፍት ውስጥ ደግሞ እንደሚገኘው ሁለትወንድማማች፣አብርሃና አጽብሐ ናቸው ። ከዚህ ጊዜ አንሥቶ የክርስቲያን ሃይማኖት ዋና ሃይማኖት ስለሆነ መስቀል የኢትዮጵያ ሕዝብ ምልክት ኾኗል ። ይህም ማለት የነገሥታቱ ትእምርት የወንድና የሴት እንዲሁም የልጅ ጌጥ እንዲሆን ከከበሩ ደንጊያዎችና ከብረት እየተሠራ ከአንገት የሚጠለቅ ከደረት የሚንጠለጠል ከጀሮ የሚሰካ ሆኗል ። በዚህ አንፃር የመስቀል በዓል ክርስቲያን በሆነውና ባልሆነው ሕዝብ መከበሩ እንደ ብርቅ ነገር ኾኖ መታየት የለበትም ።

የክርስትናን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ከኢትዮጵያዊነት ጠባይ ለይቶ ለማየት በጣም አስቸጋሪ ነው ። የኢትዮጵያዊነትን መታወቂያዎች አጣምሮና አዳምሮ የምናገኘው ክርስቲያንነትን ነው ። ይህም ማለት የክርስትና ሕይወት ጠልቆ ሰርጎ በኢትዮጵያ ገብቷል ። ስለዚህ ክርስትና እስከዚህ ነው፤ወይም ከዚህ ወዲህ ነው ብሎ ገደብ ለማበጀት ያስቸግራል ። ምናልባት እዚህ ላይ ጥቂት ማብራራት ቢያሻ የክርስትና ተጽዕኖ በክርስቲያኖች ላይና በእነርሱ አካባቢ ብቻ ነው ለማለት አይቻልም ። ቤተ ክርስቲያን የሚቆይና የማይታይ ህልውና እንዳላት ሁሉ ርቱዕና ኢርቱዕ ተጽዕኖ አላት ። በሚታይ ህልውናዋ በአመኑ ተከታዮቿ ላይ ተጽዕኖዋ ይታያል ። በማይታየው ኃይሏ ደግሞ ኢአማንያን በሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ ይፈነጠቃል ። በዚህ አኳኋን ማንም ኢትዮጵያዊ ከዚህ ተጽዕኖ ውጭ ሊሆን አይችልም ። ይሁንና «ኮከብ ከኮከብ ይበልጣል «እንደሚል መጽሐፍ የተጽዕኖው ደረጃ የተለያየ ሊሆን ይችላል ። እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ የሚለው ጥያቄ እዚህ ላይ ሥፍራ አለው ።



እንደሚታወቀው ሁሉ ሃይማኖት የኅሊናን ፍላጎት የሚያረካ አንድ ምንጭ ነው ። ነፍስ በባሕርይዋ ሃይማኖታዊ ናት ። ይህን መሠረታዊ ድንጋጌ ማንም አያፈርሰውም ። በከዋክብት የተጌጠው ሰማይ በዕፀዋትና በጽጌያት ያሸበረቀች ምድር ይህን ጉዳይ በየዕለቱ በየሰዓቱ ለእያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር ያውጃሉ ። ነፍስም በእዚህ ረክታ ምስጋናዋን ለፈጣሪዋ ታቀርባለች ። የሃይማኖት ዋናው ተግባሩ ፍጡርን ከፈጣሪው አገናኝቶ መልካም ሁኔታን መፍጠርና ማቆየት ነው ። በተለይ ክርስትና የፍቅር ሃይማኖት መባሉን በዚህ አጋጣሚ መጥቀስ ይገባል ።

የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ተግባሩ ይህ ብቻ አይደለም ። አእምሮን በማነጽ የአስተሳሰብን አቅጣጫ ለውጦታል ። ሌላ አነጋገር ክርስትና የሰውን ሕሊና ብቻ ማርካት ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተሳሰብ ሌላ አቅጣጫ ሰጥቶታል ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልቡ ብቻ ሳይሆን የተለወጠው አስተሳሰቡና አኗኗሩ ሁሉ ጭምር ነው ። የዚህ ለውጥ ተፅእኖ እምነቱን በተቀበሉት ብቻ ሳይሆን የተወሰነው ክርስትናን ባልተቀበሉም መካከል አስተጋብቷል ። እዚህ ላይ ነው የኢትዮጵያ ክርስትና ከሌሎች አገሮች የሚለይበት።የሕሊናን ፍላጎት በማርካት ብቻ ሳይወሰን የሐሳብንም አቅጣጫ ለውጧል።በዚህ ምክንያት ነው የክርስትና ሃይማኖት ጸንቶ በኢትዮጵያ የኖረው ።

## ፩/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደኅንነት ከመጣርና ከመሥራት አልተቆጠበችም ። እንደ ሃይማኖት ድርጅት ኅሊናን ለማርካት ያለባትን ኃላፊነት ስታከናውን በሌላ ደግሞ ዕውቀትን በማስፋፋትና በማከማቸት ያደረገችው ተጋድሎ በጣሙን ከፍ ያለ ነው ። እዚህ ላይ ከብዙ በጥቂቱ መጥቀስ ተገቢ ይመስለናል ።

### ሀ/ ትምህርት

በኢትዮጵያ በገዛ ቋንቋችን ትምህርት የሠመረው ክርስትና ከተሰበከ ወዲህ ነው ። ለፊደላችን አናጋሪ ምልክቶች ተገኝቶለት መጻፍ የተጀመረው ከዚያ ወዲህ ነው።በፊት ያለአናጋሪ ምልክት በግዕዙ ብቻ በመጻፍ አንባቢን ያስቸግር እንደ ነበረ ሥውር አይደለም ። አናጋሪ ምልክቶች ከተገኘለት በኋላ ግን ያለ ችግር ማንም ሰው በቀላሉ የሚያምንበት ዘዴ ተገኘ ። በዚያኑ አንፃር ደግሞ ቋንቋው በቃላት እየበለጸገ የሄደውና ብዙ ጽሑፎችም መጻፍ የጀመረው ክርስትና በኢትዮጵያ ከገባ ወዲህ ነው ። በፊት የጽሕፈት መሣሪያ ጠንካራ የሆኑ ነገሮች ሸክላ ደንጊያ ብረት የመሳሰሉ ነበሩ ። በኋላ ግን በታናሽ እስያ የታወቀና የተለመደው የመጻፊያ መሣሪያ ብራና የሚባለው የአወጣጡ ዘዴ በኢትዮጵያ ታውቆና ተለምዶ የመጻፊያ አገልግሎቱን መስጠት ጀመረ ። ከዚያ በኋላ ነው መጠናቸው ትልልቅ የሆኑ መጻሕፍት በኢትዮጵያ መጻፍ የጀመሩት ።

ክርስትና ከተሰበከ በኋላ የትምህርት ነገር ተጠቃሎ በሙሉ በቤተ ክርስቲያን እጅ ሆነ።ለአስተማሪዎችም ካህናት የመማሪያ መጻሕፍት የሃይማኖት መጻሕፍት ሆኑ ። መምህራን የሰውን ልጅ አእምሮ ቀስ በቀስ ማደግን የተረዱ ስለሆኑ የመማሪያ መጻሕፍትን በየደረጃው አዘጋጁ ። ሕፃናትም በቀላሉ የሚማሩበትን ዘዴ አቅርበዋል ። የትምህርትንም አሰጣጥ በሦስት በ፩ኛ ደረጃ ፤ በ፪ኛ ደረጃና በከፍተኛ መድበው ሲሠራበት ኖሯል ። በመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያን በጎበኙ የውጭ አገር ሰዎች በኢትዮጵያ በዋና ዋና ሥፍራዎች ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸውን ይገልጻሉ ። የኢትዮጵያ የትምህርት አሰጣጥ እስከ ያዝነው ምእት ድረስ በጠቅላላው በሀገሪቱ ሲሠራበት ቆይቶ በያዝነው ምዕት መጀመሪያ ላይ ግን መንግሥት የራሱን ትምህርት ቤት አቋቁሟል ። ይህም ሲባል የቤተ ክህ



www.ethiopianorthodox.org

ነት ትምህርት ቤት የተቋረጠ ሳይሆን በበኩሉ እንደቀጠለ ነው።በእያንዳንዱ ገጠር ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ቢያንስ ቢያንስ አንድ የንባብ ትምህርት ቤት አይጠፋም ። በዚህ አኳኋን በሀገሪቱ ወደ 15000 የሚጠጉ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ ይህንኑ ያህል ትምህርት ቤቶች አሉ ማለት ነው ።

ለእያንዳንዱም ትምህርት ቤት በማዕከላዊ ግምት ፲፭ ተማሪዎች ብንመድብ በአንድ ጊዜ 225000 ተማሪዎችን ቤተ ክርስቲያን ታሠለጥናለች ማለት ነው።በዚህ አኳኋን ትምህርትን በኢትዮጵያ ለማዳረስ ያላት ችሎታ ከፍ ያለ ነው ።

መምህራን ለሚሰጡት ሰፊ አገልግሎት አብዛኛውን ጊዜ አይከፈላቸውም አንዳንዴም ቢከፈላቸው ከዕለት ጉርሳቸው ከዓመት ልብሳቸው አይበልጥም ። አንዳንዴም በእጅ ጥበብ ማለት፤መጽሐፍ በመጻፍ ፤ ድጉስ በመደጎስ ፤ ሸማ በመሥራት፤ ራሳቸውን በመርዳት አገልግሎታቸውን በነፃ ከመለገስ አይቆጠቡም ። በእንዲህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን የትምህርት መሳተፊያ ገቢታ ሁና ተርታውን ለ፲፮ ምእት ዓመታት ቆይታለች ።

## ለ/ ሥነ ጽሑፍ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት እንብርት ናት ከተባለ፤የሥነ ጽሑፍ መደብር መሆኗ የታወቀ ነው ። ቅዱሳት መጻሕፍትን፤በጠቅላላው የሃይማኖት መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን የታሪክ ፤ የባሕረ ሓሳብ ፤ የፍልስፍና ፤ የሕግና ይህን የመሳሰሉትን መጻሕፍት ግማሾቹ እየተተረጐሙ እየተጻፉ ሲገለገልባቸው ቆይቷል ።

ምንም እንኳን ብዙዎቹ በግዕዝ የተጻፉ ቢሆኑ አንዳንዶቹ በአማርኛ ተደርሰዋል፤ወይም ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል ። የአማርኛ ቋንቋም የሀገሪቱ ዋና መናገሪያ ሆኖ እንዲሠራበትና እንዲስፋፋ የረዳች ቤተ ክርስቲያን ናት ። የሀገሪቱ የሥነ ጽሑፍ ክምችት በሚገባ በመከባከብ በብዙ ቅጂዎች ካህናት እያባዙ እንዳይጠፉ አድርገዋል ። በዘመነ ስደትም ጊዜ እንዳይቆነጻጸሉ ከማይደፈር ዋሻ ውስጥ ከማይወጣ ደብር ላይ በመሸሸግ አድኗቸዋል ። ዛሬ ኢትዮጵያ አለኝ የምትለው በእንዲህ ዓይነት ዘዴና ጭንቀት የቆየውን ሥነ ጽሑፍ ነው ።

## ሐ/ኪነጥበብ

ተግባረ እድ በማንኛውም መልኩ የሚገኘው፤ተጠብቆም የኖረው፤በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ። የግርግዳ ሥዕሎች፤ የመጻሕፍት ሐረጐችና ንድፎች፤ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ላይ የተቀረጹ ቅርሶች፤በጠቅላላው ባለፉት ብዙ ምእት ዓመታት የተከማቹ የእጅ ሥራዎች የሚገኙት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ። ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ በትግሬ ከቋጥኝ የተፈለፈሉ አብያተ ክርስቲያናትና በውስጣቸው የተሣሉት ሥዕሎች ፤ በሮሀ የተሠሩት የቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት «ስምንተኛው የዓለም ተአምር» በመባል በብዙ የውጭ አገር ሰዎች ዘንድ የታወቁትን ማስታወስ ይበቃል ። አንድ አገር ጐብኝ የረቀቀውንና የተዋበውን የኢትዮጵያ እደ ጥበብ የሚያይባቸው እሊህና ሌሎችም ተመሳሳይ ታሪካዊ ሥፍራዎች ናቸው ።

## መ/ የታሪክ ቅርሶች

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም የጥንት ቅርስ ጠብቃ ያቆየች ናት ። ንግሥታት ዘውዶች ፤ የክብር ልብሶች ፤ የመሳፍንት የራስ ወርቆች ፤ የጦር መሣሪያዎች እንዲሁም ብዙ ልዩ ልዩ የወግ ዕቃዎች በታላላቅ አድባራትና ገዳማት ተጠብቀው ቆይተዋል ። በእዚህም ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ ክርስቲያን ያልሆኑ የኢትዮጵያ



ታላላቅ ሰዎች ዕቃዎችን ጭምር ነው።ለምሳሌ ደብረዳሞ ትግሬ አያሌ የእስላም የወርቅና የብር መሐለቆች፤እንዲሁም የዓረብ ጽሑፍ ያለባቸው የሀር ጨርቆች በሚገባ ተጠብቀው ይገኛሉ ። በመርጡለ ማርያም የአሕመድ ግራኝ ልብስ በክብር ተቀምጧል።ደብረ ወርቅ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን በ፲፭ኛው ምዕት የወጋው የበደላይ ጥሬር ይገኛል።

## ፫/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በወል የሕዝብ መሆኗ የሚታወቀው በማኅበራዊ ኑሮ በምትፈጽመው ተግባሯ ነው ። በዓይነቱ ቤተ ክርስቲያን ማንኛውም የማኅበራዊ ኑሮ ክንውን የሚፈጸምባት ናት ። አንዱ ለአንዱ በሚገባ የሚተዋወቅበትና ወዳጅነት የሚመሠርትበት ከቤተ ክርስቲያን አጸድ ውስጥ ነው።አብሮማኅበር የሚጠጣ ሰው አይጣላም፤ ቢጣላም ዳኛ አይሄድም ማኅበረተኞቹ ያስታርቃሉ ። እሑድ ከቅዳሴ ውጭ እንዲሁም አንዳንዴም በአዘቦቱ ቀን የተጣላ ማስታረቂያ ነው ። በዕድሜ የገፉ አባቶች ተመርጠው በአጥቢያቸው የተፈጸመውን አለመግባባት ዳኛ ከመድረሱ በፊት ለማብረድ ይሞክራሉ ። በባልና ሚስት በርስት እንዲሁም በሌላ የሚነሣውን ጠብ ተመልክተው አካክሰው ያስታርቃሉ ።

ቤተ ክርስቲያን የነዳያንና ተስፋ የሌላቸው ሰዎች መጠጊያ ናት ። ዕጓለማውታ የሚያድጉት ፤ ሕሙማን የሚያርፉት ፤ ሽማግሌዎች የሚጦሩት ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ነው ። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኙት መቃብር ቤቶች ለዚህ ሥራ ያገለግላሉ ። ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን ርዳታ እየጠየቀች ችግረኞችን ትረዳለች ።

ሌላም አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ትፈጽማለች ። የመንፈሳዊ በዓላቶችዋ የሕዝብም በዓላት ናቸው ። ቅዱስ ዮሐንስ ፤ መስቀል ፤ ገና ፤ ጥምቀትና ፋሲካ የወል የሁሉም በዓላት ናቸው።እሊህ ቀናት የዕረፍትና የመዝናኛ ቀናት ናቸው ። ሕዝቡ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እየተሰበሰበ በእስፖርትና በዘፈን ሲዝናና ይውላል ።

## ፬/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቀውጢ ቀን

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመቸውም ይልቅ አስፈላጊነቷ በችግር ጊዜ ነው ። ይህች ሀገር ለብዙ ዘመናት ነፃነቷን ጠብቃ በጠላቶቿ ታፍራ የኖረች ናት። መላው የአፍሪቃ ክፍለ ዓለም በተገዢነት ጨለማ ሲኖር ኢትዮጵያ ብቻ የነፃነቷን ፋና እንደጨበጠች ኖረች። ለእዚህም ዋናው ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ናት።የሕዝቡን አንድነት ጠብቃ ወታደሩን እያበረታታች ነፃነቱን እንዲከላከል በማድረጓ ነው ። በእዚህ በኩል የፈጸመችው ድርሻዋ በጸሎትና በማስተማር ብቻ ሳይገታ በጦር ሜዳም በመገኘት ብዙዎች ካህናትና መነኮሳት ራሳቸውን ሠውተዋል ። ለእዚህም ሩቅ ሳንሔድ የቅርቡን የኢትዮጵያን ታሪክ ብንመለከት በድርቡሽ ወረራ ፤ በዓድዋ ጦርነት ፤ በማይጨው ውጊያ ፤ በአምስት ዓመቱ የጠላት ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ተጋድሎና መሥዋዕትነት ለአርአያነት የሚጠቀስ ተግባር ነው ። ጳጳሳት ፤ ካህናት ፤ መነኮሳት በሰማዕትነት ተጋድሎ ፈጽመዋል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በ፳፡ቱ የመከራ ዘመን ከአርበኞች ጋር በዱር በገደል ከስደተኞች ጋር በሰው አገር ስትንከራተት ኖራለች ። በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በምንም ዓይነት በማንኛውም ጊዜ ከሕዝቡ የተለየችበት ወቅት የለም ። እንዲህ ዓይነቱ የቤተ ክህነት ትብብር ባይኖር ኑሮ ኢትዮጵያ የድልን አክሊል ተቀዳጅታ ይህን ያህል ዘመን በነፃነት ትኖር ነበር ብሎ ለመገመት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፮/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ሥልጣን

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱን ትምህርትና ቅርስ ጠባቂ መሆንዋ ቀደም ብሎ ተነግሮአል ። ይህ ኃላፊነትዋ ሁል ጊዜ አዲስ ነገርን እንድትሻ አድርጓታል ። በኪነ ጥበብ በኩል ያለውን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆነ የአንድ ዘመን የአሠራር ዘዴ ከሌላው ጋር አይገጥምም ። የተሻሻለ ሌላ የላቀ ጥበብ ታክሎበት ይገኛል ። በሥዕልም እንዲሁ ነው ። የየዘመኑን ንድፍና አጣጣል ብናነጻጽር ልዩነትን እናያለን ። በቅኔም እንዲሁ ነው። እያንዳንዱ ባለቅኔ የደረጃው መጠን ይለያይ እንጂ የራሱ አስተሳሰብና የቅኔ ስሜት አለው ። አንዱ የሌላውን መቅዳት ነውር ነው ። ስለዚህ አዲስ ጥበብ አዲስ ተኪንዎ አይጠላም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገሥታቱ ከአውሮጳ የእጅ ሥራ ዐዋቂዎችን ፤ ሠዓሊዎችን ፤ መሐንዲሶችን ወዘተ እንዲጠይቁ የምታበረታታና የምትረዳ እርሷ ነበረች። ደብዳቤዎችን አርቀው ጽፈው ይዘውም በመልእክተኝነት የሚሄዱት ካህናት ነበሩ ። በሀገር ውስጥ ያሉትም ባለእጆችና ጥበበኞችን ምንም ሃይማኖታቸው የተለየ ቢሆን አክብራ በሙያቸው እየተጠቀመች ኑራለች ።

በምዕራብ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አዲስ ሐሳብንና ሥራን በመቃወም ግጭት አትርፋለች ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ግጭት ሳይሆን የሚያሳየው ተካፋይነቱን ነው ። እሩቅ ሳንሄድ በቅርብ በአዲስ ዘመን ታሪካችን በሆነው የኑሮ ለውጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞ ድምጽ ያሰማችበት ጊዜ የለም ። አዲስ ትምህርት በአገራችን ሲጀመር ተካፋይ ለመሆን ጠየቀች እንጂ የዓላማው ተቃዋሚ አልሆነችም ከአዲሱ ሥልጣኔ የተገኘውን ውጤት ከመቀበልና ከመጠቀም ወደኋላ አላለችም ። ሁናቴውን በደንብ ያላመዛዘኑ ሰዎች ነቀፌታ ይደረድራሉ ። አንዳንዶቹ ለምን አሁንም ቢሆን አትመራም በሚል አባባል ተነሣሥተው ይሆናል ። ይህም ቢሆን አግባብ አይደለም ። ቤተ ክርስቲያን በዓለማዊው ኑሮ ይህን ያህል ፊት ቀደም ሁና መገኘቱ ተፈላጊም ተገቢም አይደለም። መሰናክል አመለሆኗ ግን ትልቅ ጸጋ ነው ።

### መደምደሚያ

ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የሚያሰኛት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቆየችው ትምህርትና የቅርስ ክምችት ነው ። ይህን ነው ኢትዮጵያ የራሴ ነው ብላ የምታቀርበው ። ይህን የቀነስነው እንደሆነ ኢትዮጵያዊ የምንለው ምን ሊሆን ነው ? ጥያቄውን መመለስ አስቸጋሪ ነው ። ይህ እንግዲህ ስለአለፈው ነው፤ ወደፊትስ ቤተ ክርስቲያን ምን ለመፈጸም ትችላለች ? ይህን ጥያቄ በአጭሩ ለመመለስ ኢትዮጵያዊነታችንን የምትጠብቅልንና የምታበረታልን እርሷ ናት ። እላይ እንደተባለውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የወል ወገኑ ናት ። እምነቱ ሌላ ይሁን እንጂ አስተሳሰቡ ኢትዮጵያዊ ነው ። በእዚህ ከቤተ ክርስቲያን ይዛመዳል ። በእዚህ አኳኋን ቤተ ክርስቲያን የአንድነት አውታር ናት ። ቤት ያለምሰሶ እንደማይቆም ቤት ክርስቲያንም በኢትዮጵያ ያላት ስፍራ ይህን የመሰለ ነው



www.ethiopianorthodox.org

### በጠቅላላ የሕግ አገልግሎቱ አማካይነት የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የሕግ አቋም ከሚያጠናው ልዩ ኮሚቴ ለቅዱስነታቸው የቀረበ

ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት የክርስቲያን ደሴት ሆና እንደመቆየቷ መጠን ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተ ሰቡ በትምህርት ሥልጣኔን በመስጠት ባህልና ታሪካዊ ቅርሶችን ጠብቃ በማቆየት በሰላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ ከመንግሥቱ ጎን በመሰለፍ ያበረከተችው አገልግሎት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው ፤ ግን ይኸው አገልግሎቷ በአዲሱ ትውልድ ዘንድ እየተረሣ የሔደ ይመስላል ፤ ይሁን እንጂ ከክርስቶስ ልደት በፊትም ሆነ በኋላ እስከ አሁን ድረስ ሆነ ወደፊትም የሠራችውንና የምትሠራውን ልትሠራውም የሚገባትን ለሕዝቡ ማስገንዘብና ማስታወስ አስፈላጊዋ ነው ።

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሰጠችው አገልግሎት በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ሲገኝ ስንኳንስ ከሷ ውጭ የሆኑ ሌሎች ቀርተው ወገኖቿ ምዕመናን እንኳን ባለመረዳታቸው ለምታቀርበው የመብትና የግዴታ ጥያቄ ተገቢውን መልስ በማግኘት ፈንታ ከሌሎቹ ጊዜ ከወለዳቸው ድርጅቶች ጋር በማወዳደር የሚተችባት ይመስላል ።

ስለዚህ የምታቀርበው ሕጋዊ ጥያቄ ሁሉ ተቀባይነትና ተደጋፊነት ያገኝ ዘንድ ወገኖቿ ምእመናንም ሆኑ ሌሎቹ ተጠያቂ እንዳይሆኑ ፤ ለጥያቄዋም ትክክለኛ ውንፍርድ ለማስገኘት እንዲቻል ይኸንን ከሀገሪቱ ህልውና ጋር ተዋሕዶ የሚገኘውን አገልግሎቷን በቀደምትነት ለወገኖቿም ሆነ ወገንነቷን ለሚሹ ሁሉ ማስታወስና ማሳወቅ ስለሚያስፈልግ ከጥንት ተያይዞ የመጣውን ታሪኳን የሚያስረዳ ልዩ ልዩ ማስረጃ ስለአላት በሬዲዮ በጋዜጣ በልዩ ልዩ ማባዣዎች እየተባዛ አሁኑን ጀምሮ እንዲገለጽ ቢደረግ ቤተክርስቲያን የምታቀርባቸው የመብትና የግዴታ ጥያቄዎች ሁሉ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ይረዳታል ብለን እምነንበታል ።

ስለዚህ ይኸው ጉዳይ በጥንቃቄ እየተዘጋጀ ለሕዝቡ እንዲገለጽ የቅዱስነታቸው ፈቃድ በአስቸኳይ አርፎበት ትእዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ ዘንድ ቢደረግ ወደፊትም ቤተ ክርስቲያን ለምታቀርበው ሕጋዊ ሐሳብ ሁሉ የሚረዳ መሆኑን በመረዳት ሐሳቡን በትሕትና እናቀርባለን ።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕገ መንግሥታዊ አቋም

# የቀረበ የማሻሻያ ሐሳብ

መሠረታዊቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ በአሳለፈቻቸው የሰላምም ሆነ የመከራ ዘመናት ሁሉ ያበረከተቻቸው መንፈሳዊና ሥጋዊ አገልግሎቶች እጅግ በጣም ከፍ የሉ መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር ነሉት ምእመናን ትምህርተ ክርስትና እንዲዳረስ ከማድረጓም ሌላ፤ ሕዝቡ በእውቀት ተሻሽሎ ድንቁርና እንዲጠፋና በማኅበራዊ ኑሮም እንዲደረጅ ያደረገችው ሰፊ ጥረት በቀላሉ አይገመትም ። የኢትዮጵያን ታሪክና ጥንታውያን ቅርሶችም ጠብቃ በማቆየት ያበረከተችው አገልግሎት ብዙ ነው ። ለሀገሩ ነፃነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሆኖ ለጦርነት በሚሰለፍበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያንም ፅላትና መስቀል ተሸክማና ግንባር ቀደምሁና ከሕዝቡ ጋር በመሰለፍ የመከራው ተካፋይ ያልሆነችበት ጊዜ አይገኝም ።

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጋር የቆየው ግንኙነት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣው ሕገ መንግሥት«መሠረታዊት ቤተ ክርስቲያን»ተብላ ተገቢ ቦታዋን ይዛለች ፤ ይሁን እንጂ በዚሁ ሕገ መንግሥት ውስጥ ስለመሠረታዊቱ ቤተ ክርስቲያን የተጻፉት አንቀጾች ያልተብራሩና ያልተሟሉ መሆናቸውን ሕገ መንግሥቱ በሥራ ላይ በቆየባቸው ዘመናት ማረጋገጥ ተችሏል ። ስለዚህ ያሉት አንቀጾች ተብራርተውና አዲሶችም ተጨምረው መሠረታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ተገቢ ቦታዋን እንድታገኝ በማሰብ ከዚህ የሚከተሉትን የማሻሻያ ሐሳቦች አዲስ በሚሻሻለው ሕገ መንግሥት ውስጥ እንዲገቡ እንጠይቃለን ።

### ተሻሽለው የቀረቡ ሐሳቦችና አንቀጾች

፩ኛ አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት በተሻሻለበት በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሪ ማዕረጉ ሊቀ ጳጳሳት ስለ ነበር በሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ውስጥ"ሊቀ ጳጳሳት„የሚለው ቃል ሁሉ እየተለወጠ «ፓትሪያርክ» የሚለው የማዕረግ ስም እንዲተካበት ።

፪ኛ ሀገረ ስብከት ያላቸው የመሠረታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባሎች ይሆናሉ፤ የሚል አንቀጽ አግባብ ባለው ሥፍራ እንዲገባ ።

### ማብራሪያ

፩፤ እስከ ዛሬ ድረስ የመሠረታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት የሕግ መወሰኛ አባሎች ሆነው እየተሾሙ ሲያገለግሉ የቆዩ ስለሆነ አንቀጽ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ በጽሑፍ እንዲጨመር ከመሆኑ በቀር እንደ አዲስ ሆኖ የሚቆጠር አይደለም ።

፪፤ ይህምዓይነትአሠራር በኢትዮጵያብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ይሠራበታል። ለምሳሌ ተመሳሳይ አቋም ያላት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ሁሉ በእንግሊዝ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት /ሐዋስ-ኦፍ-ሎርድስ/ አባሎች በመሆን ይሠራሉ ።

፫ ፤ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱስ ማርቆስ ትምህርት መሠረት የተቋቋመችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መሠረታትዊ ቤተ ክርስቲያን ናት ። ስለዚህም በመሠረቱ የተደገፈች ናት ። የንጉሠ ነገሥቱ ሃይማኖት ሁል ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሆን አለበት ፤ መንፈሳዊ አገልግሎትም በሚደረግበት ሁሉ የንጉሠ ነገሥቱ ስም ይጠራል ።

### ማብራሪያ

አንቀጽ ፻፳፮ ምንም ዓይነት ማሻሻያ አልተደረገበትም ።
አንቀጽ ፻፳፯

፬ ፤ ሀ ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት ፤ ሊቃነ ጳጳሳት አባሎች በሆኑበት ቅዱስ ሲኖዶስ ትተዳደራለች ።

ለ ፤ ፓትርያርኩ ፤ ሊቃነ ጳጳሳቱ ፤ ጳጳሳቱና ኤጲስ ቆጶሳቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመክሮበት በንጉሠ ነገሥቱ በሚጸድቀው የምርጫ ሥነ ሥርዓት መሠረት ከካህናትና ከምእመናን በተውጣጣ የምርጫ ጉባኤ ይመረጣሉ ።

ሐ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ምርጫውን ሲቀበለውና ሹመቱን ሲፈቅድ መንፈሳዊ የተቀብዖ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ይፈጸምላቸዋል ።

መ፤ የመሠረታዊቱ ቤተ ክርስቲያን የውስጥ አስተዳደርና መንፈሳዊ ነክ ደንቦች ፤ ትእዛዞችና ውሳኔዎች ሁሉ በቅዱስ ሲኖዶስ እየተመከረባቸው በቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በፓትርያርኩ ይታወጃሉ ።

ሠ ፤ ከዚህ ውጭ ያለው የቤተ ክርስቲያን ሥጋዊ አስተዳደርና ድርጅት ሕጎች በቅዱስ ሲኖዶስ እየተወሰኑ በንጉሠ ነገሥቱ በነጋሪት ጋዜጣ ይታወጃሉ ።

ረ ፤ በቤተ ክርስቲያን ሥጋዊ አስተዳደር ቅዱስ ሲኖዶስን የሚረዳ ጳጳሳት ፤ ካህናትና ምእመናን በአባልነት የሚገኙበት አንድ የቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ በሕግ ይቋቋማል ።

### ማብራሪያ

አንቀጽ ፻፳፯የመሠረታዊቱ ቤተ ክርስቲያንን ሥጋዊና መንፈሳዊ አስተዳደር የሚመለከት ስለሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አስተዳዳሪ ቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑንና የፓትርያርኩ ፤ የሊቃነ ጳጳሳቱ ፤ የጳጳሳቱና የኤጲስ ቆጶሳቱ የአመራር ሥነ ሥርዓት የተብራራ ሆኖ ቅደም ተከተሉ ተገቢ ቦታውን ከያዘ በኋላ ምእመናንም በቤተ ክርስቲያኗ ሥጋዊ አስተዳደር ተካፋይነት እንዲኖራቸው ተደርጓል ። ሆኖም የአንቀጹ መሠረተ ሃሣብ አልተለወጠም ።

፭ ፤ ሀ ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችና የጥንታዊ ቅርስነት ዋጋ ያላቸው ንዋየ ቅድሳትና የቤተ ክርስቲያን ንብረቶች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሀብት ሁነው በቤተ ክርስቲያኗ ይጠበቃሉ ።

ለ፤ ቤተ ክርስቲያን የምታምንባቸው የተቀደሱ ነገሮች ሁሉ በሕግ ልዩ ጥበቃ ይደረግላቸዋል ።

### ማብራሪያ

ሀ ፤ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ የሚገኙ ጥንታውያን የታሪክ ቅርሶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ትሠራባቸው የነበሩ



www.ethiopianorthodox.org

ትና አሁን የምትሠራባቸው ንዋየ ቅድሳት ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት አልባሳትናሌሎችም የም ሥጢራት ዕቃዎች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የተሠራባቸው ጥንታውያን የታ ሪክ ቅርሶች ስለሆኑ በይዞታዋ ተጠብቀው ለትውልድ ይተላለፋሉ ፤ እነዚህም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የታሪክ ቅርሶች ሳይሸጡና ሳይለወጡ እስከ ዛሬ ድረስ መቆየት የቻሉት በቤተ ክርስቲያን ጠባቂነት መሆኑ ሊታወስ ይገባል ።

የቤተ ክርስቲያናችን እምነት መሠረት የሆኑትን ጽላትና ሌሎችም የምሥጢ ራት ዕቃዎች በእለት ጥቅም ፈላጊዎችና በሌቦች እየተሰረቁ በመሸጣቸው ጥንታውያን የታሪክ ቅርሶች ከመጥፋታቸውም ሌላ በአማኙ ሕዝብ ዘንድ ጭቅጭቅ እየፈጠረ የሀገርን ፀጥታ ስለሚያደፈርስ በሕግ ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ያስፈልጋል ።



# ኑ ቅ ዕ ን ጹ ሕ

ኢትዮጵያ መሠረታዊ እምነቷና ሥርዓቷ ከጥንት ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ፤ ኋላም በዘመነ ሐዲስ በመጀመሪያዎቹ ፤ ዓመታት በክርስትና እምነት በሕፅዋ ለሕንደኬ አማካይነት በፈቃደ እግዚአብሔር በፊልጶስ እጅ የተቀበለች ስትሆን ፤ የኢ. ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በ፬ኛው መቶ ዓመት በተሟላ ሁኔታ ተሠርታና ተቋቁማ በየዘመናቱ ለተነሡት ለነገሥታቱ ፤ ለመሳፍንቱ ፤ ለመኳንንቱ ፤ ለሠራዊቱና ለሕዝቡ በየመልኩ ፤ መንፈሳዊ አገልግሎቷን ስታበረክት ፤ የበጎ ሥራ ፤ የትምህርትና የዕውቀት የባህልና የጥንታዊ ቅርስ መገኛ ሆና ኖራለች ።

በማናቸውም ዘመንና በማናቸውም ዓይነት የኑሮ ሁናቴ የሚገኘው ትልቁም ትን ሹም ፤ የተማረውም ያልተማረውም ፤ ገበሬውም ነጋዴውም ፤ ወታደሩም ፤ የዕለት ሙያ ተኛውም «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ፤ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ» ተብሎ የተጻፈውን በመከተል ፤ ሁሉም በሥጋውም በነፍሱም፤ የሚገባውን እየ ሠራ በፍቅርና በሰላም እንዲኖር ተግባሯን ስትፈጽም ኖራለች ።

ድሀ ሲበደል ፤ ፍርድ ሲጓደል ፤ የውስጥ ፀጥታና አስተዳደር ሲቃወስ ፤ ዝም ብላ አትመለከትም ። ሕገ እግዚአብሔርን ቃለ ወንጌልን መሠረት አድርጋ ትመክራለች ፤ ታስተምራለች ፤ ታስጠነቅቃለች ። በመንግሥትና በሕዝብ ፤ በገዥና በተገዥ ፤ በሰዎ ችና በሰዎች መካከል እየተገኘች ሁሉንም ወገኖች ታስማማለች ። የሕዝቡን አንድነት ፤ የሀገሪቱን ሰላምና ፀጥታ ፤ የመንግሥቱን አቋምና ፀናት ፤ ብሔራዊውን ነፃነትና ግዛት መሠረታዊውን ሃይማኖትና ባህል የሚቃረን ፤ የውስጥም ሆነ የውጭ ጠላት ሲነሣ ቀዳሚ ሆና የምትጋደል ቤተክርስቲያን ናት ። ይህንንም የማይታበለውና የማይጠፋው የታሪክ መዝገብ እያረጋገጠ ሲመሰክር ይኖራል ።

ከዚህ ዘመን ለደረሰችው ኢትዮጵያ ለህልውናዋና ዛሬ ላለነው ኢትዮጵያውያን አኗኗር ቤተክርስቲያን ያበረከተችው ድርሻ በከፍተኛ የሚገመት መሆኑ በማንም ዘንድ የሚታወቅ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፣ ለዚህ አገልግሎቷ ከመንግሥትና ከሕዝብ፤ ከኅብረተ ሰብና ከግል ሰዎችም የሚያስፈልጋትን መገልገያ እያገኘች በዚሁ አገሪቱንና ሕዝቡን ስታገለግል ኑራለች ። ከዚህ ውስጥ ሁል ጊዜ በውስጥም ሆነ በውጭ ጎልቶና በልዩ ልዩ መልክ ተደጋግሞ የሚነገረው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲሶ መንግሥት አላት የሚ ለው ታሪክ ነክ የሆነው ዘይቤ ነው ።

በታሪክ ተመዝግቦ እንደሚነበበው ይህ የሲሶ መንግሥት ስጦታ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተደረገው በ፲፫ኛው መቶ ዓመት ዓፄ ይኩኖ አምላክ ለደብረ ሊባኖስ ዕጨጌ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በገቡት ቃል ኪዳን ነው ።

ከንጉሥ ሰሎሞን ዘር ከወረደው የትውልድ ሐረግ የተገኘው ይኩኖ አምላክ ከዛጌዩ መንግሥት ከተወለደው ከዓፄ ነአኵቶ ለአብ ዙፋኑን በሰላማዊ ውል ባስመለሰ ጊዜ ይህ ንን ውል በሰላም ያስፈጸሙና ለዚህ ዕድል ያበቁት አቡነ ተክለሃይማኖት ስለነበሩ ለዚህ ውለታ ለቤተክርስቲያን መገልገያ ለካህናት መተዳደሪያ የሚውል ዓፄ ይኩኖ አምላክ የመንግሥቱን ሲሶ ሰጥቻለሁ ብለው ቃል ኪዳን መግባቱ በታሪክ ተጽፎ ይገኛል ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህንኑ የሲሶ መንግሥት ስጦታ ሥሪቱንና አፈጻጸሙን ለመመርመር የቤተክርስቲያንን አቋምና አስተዳደር መመልከት ያሻል ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ፤ የስም አጠራሯ አንዲት ትሁን እንጂ በውስጥ አስተዳደሯ ፤ ገዳማት፤አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በሚል መልክ በውስጧ ተቋቁመው ራሳቸውን ችለው ፤ ሲሠሩ ይገኛሉ ። ነገሥታቱና መሳፍንቱ ፤ ገዳማትንና አድባራትን ለመርዳት ሲሉ በዓዋጅ አጽድቀው ሲያቋቁሙ ፤ ሕዝቡና ባላባቱም ከመንግሥት እያስፈቀዱ በየገጠሩ ቤተክርስቲያን ሲሠራ ፤ መተዳደሪያና መገልገያ የሚሆን መሬት ይሰጣሉ ። ይህ መሬት እንደየሁኔታው ለየተሰጠው ገዳም ፤ ደብርም ሆነ ገጠር ቤተክርስቲያን የግል ሀብቱ ንብረቱ ይሆናል ። አንዱ የሌላውን መብት ተላልፎ መንካት አይችልም ። ወይም ቤተክህነትም ሆነ ሌላ ባለሥልጣን ያንዱን ገዳም ፤ ደብር ወይም የገጠር ቤተክርስቲያን መብት ሊይዝ ወይም ለሌላ ሊያዛውር አይችልም ።

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የሚገለገለው ርስቱ በሕዝብ የተያዘ ቢሆንም ከአገልጋዮቹ ካህናት አንድአንዶቹ መሬቱን በልዩ ልዩ መልክ ይዘው ራሳቸው እያረሱ ወይም እያሳረሱ ከዚያ መሬት በሚገኘው ሰብል በመጠቀም የሚያገለግሉ አሉ።የአንድነት ገዳም የሆነ እንደሆነ መነኮሳቱና መናንያኑ ያንን ለገዳሙ መተዳደሪያ የተሰጠውን መሬት ራሳቸው እያረሱ ወይም እያሳረሱ ርስትነቱ የገዳሙ ሆኖ ይጠቀሙበታል ።

በጥንተ ሥሪቱ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሲተከል የተሰጠው ፤ መተዳደሪያ መሬት ለካህናቱ እንደደመወዝ ተቆጥሮ በሪምነት ፤ በማደሪያነትና በልዩ ልዩ መልክ በግብዝና ፤ በቅስና ፤ በዲቁና ፤ በድብትርናና ይህን በመሳሰለው ፤ የአገልግሎት ስያሜ ሲደለደል የካህን ልጅ ካህን ያልሆነ እንደሆነ በዚሁ ሁኔታ የተሰጠውን መሬት የዚያ ካህን ተወላጆች ይዘው ለሚያገለግል ካህን ተገቢውን አበል እየከፈሉ ያስገለግሉበታል ። ራሳቸውም ይጠቀሙበታል ። ይህን የመሰለው የቤተክርስቲያን መገልገያና የካህናት መተዳደሪያ መሬት የሰሞን መሬት ይባላል ።

ስለቤተክርስቲያን አስተዳደር ፤ በ፲፱፻፴፬ ዓ ም በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በወጣው ደንብ ላይ ስለቤተክርስቲያን ርስት ዝርዝር የሚገልጸው አንቀጽ እንዲህ ይላል ። የቤተክርስቲያን ርስትና ጉልት ዓይነቱ ብዙ ነው ። ለቤተክርስቲያን መገልገያ ለካህናት የተሰጠ ሪም ወይም ቀላድ የሚባል ርስት አለ ። ለአለቆችና ለገበዞች የተሰጠ ገባርና መልከኝነት ወይም ቀላድ መሬት አለ ። መኳንንትና ወይዛዝርት ሌላው ሕዝብ ሁሉ የገዛ ርስቱን በመንግሥት ፈቃድ እያዛወረ ወደ ቤተክርስቲያን ያገባው ርስት አለ ። ይህንንም የመሰለው በአንድነት ተጠቃልሎ የቤተክርስቲያን ርስትና ጉልት ይባላል ።

ከዚሁም ግብሩን ለቤተክርስቲያን እየከፈለ ለማስገልገል የገዛ ርስቱን በመንግሥት ፈቃድ እያዛወረ ወደቤተክርስቲያን ካስገባው ሰው በስተቀር ሌላው ለቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ እንዲሆን ከመንግሥትም ሆነ ከግል ሰዎች የተሰጠው የሰሞን መሬት በመሠረቱ ርስትነቱ የዚያ ገዳም ፤ ደብር ወይም ቤተክርስቲያን በመሆኑ ፤ መንቀያ መትከያ ሆኖ በጊዜው በግንባር ለሚያገለግለው ካህን ፤ እንደደመወዝ በሪምነት ወይም በማደሪያነት የሚሰጥ ነው ።

አሁን ባለው ሁኔታ ይህን የመሰለው የቤተክርስቲያን የሰሞን ፤ መሬት በግንባር በሚያገለግሉ ባንዳንድ ካህናት እጅ ከሚገኝ በቀር አብዛኛው በወንድ መኰንን ፤ በሴት ወይዘሮ ፤ በነጋዴውም ሆነ በወታደሩ ፤ በአራሹ ገበሬና በማንኛውም ሰው እጅ ገብቶ እየታረሰ ሕዝቡ የሚጠቀምበት ሆኖ ይገኛል ። ይህ የሰሞን መሬት ሥሪቱ ባይፋለስ እንኳ በግዥ ፤ በውርስ በስጦታ ካንዱ ወደሌላው በተፈለገው ዓይነት ለማንም ሊዛወር የሚችል ሆኗል ። ስለዚህ በአጠቃላይ አነጋገር ለቤተክርስቲያን ፤ የተረፋት ስሙ ፤ ይኸ



ውም የሰሞን መሬት መባሉብቻ ነው።ማለት ነው።የሰሞን መሬት ተብሎ ከሰሞን መሬት የሚገኘው ግብር የተሰበሰበ እንደሆነ ከዚያ የሚጠራቀመውን ገንዘብ ብቻ ነው ቤተክርስቲያን ትጠቀምበታለች ሊባል የሚቻለው ።

እንዲህ ከሆነ የሲሶ መንግሥት ስጦታ ቃል ኪዳን በምን ዓይነት ሁኔታ ተተርጉሞ ከሥራ ላይ ሊውል ይችላል ፤ ከዚህ ጋር አብሮ ሊታሰብ የሚገባው ሲሶ ለነጋሽ ፤ ሲሶ ለአንጋሽ ፤ ሲሶ ለቀዳሽ የሚባለው ታሪካዊ ዘይቤ ነው ፤ በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት ሥሪት ይህን የመሰለ ጥንታዊ ታሪክ ሲተረክ ይገኛል ይሰማል ።

ስለዚህ የሲሶ መንግሥት ቃል ኪዳን ጥንታዊውን የታሪክ መዝገብ ይዞ የሚገኝ እንጂ ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዛሬ ካለው የመንግሥት ገቢ ላይ ሲሶውን አግኝታለች ወይም ታገኛለች ማለት አለመሆኑንና ቤተክርስቲያን ባሁኑ ጊዜ እንኳንስ የመንግሥቱን ሲሶ ገቢ ይቅርና ከመቶ አንዱን እንኳ የማታገኝ መሆኗን ከዚህ በላይ ባጭር የተሰጠው ሐተታ በቀላሉ ሊያስረዳ ይችላል ።

፪ኛ/ ቤተክህነት ተብሎ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን አስተዳደር እያስተባበረ እንዲመራ ከቅርብ ዘመን ወዲህ የተቋቋመው መሥሪያ ቤት የሰሞን መሬቶች በትክክል እንዲመዘገቡና ከሰሞን መሬት የሚገኘውም ዓሥራትና ግብር እየተሰበሰበ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ።

እንደሌላው የግል መሬት ሁሉ የቤተክርስቲያንም የሰሞን መሬት ማንኛውም ዓይነት ግብር ይከፈልበታል ፤ አንድ ጋሻ መሬት ያለው ሰው በመሬቱ ለመንግሥት የሚከፍለው ግብር አራት ዓይነት ሲሆን ፍሬ ግብር ፤ ቀድሞ ዓሥራት ይባል በነበረው የተተካው የርሻ ጥቅም ግራር ፤ የትምህርት ግብር የጤና ግብር የሚባሉት ናቸው ። ቤተክርስቲያን ቀድሞ በዳኝነት ፤ በገበያ ቀረጥና በመሳሰለው ስታገኝ የነበረው ገቢ እንዲቀርባት ሲደረግ በዚህ ምክንያት ከሰሞን መሬቶቿ የሚሰበሰበው ቀድሞ ዓሥራት ዛሬ የርሻ ጥቅም የሚባለው ግብርና የትምህርት ግብር ተፈቅዶላት ራሷ እየተቀበለች ከሞላ ጎደል ስትሠራበት የነበረው አሠራር ቀርቶ አሁን ከሰሞን መሬቶች የሚገኘውን የርሻ ጥቅም ግብሩን ከ፲፱፻፷፰ ዓ ም ጀምሮ የገንዘብ ሚኒስቴር እየሰበሰበ እንዲሰጣት ተደርጎ ከሞላ ጎደል በሚገኘው ገቢ በዚህ መልክ ይሠራል።ፍሬ ግብር የተባለውን ግን ቤተክርስቲያን አትቀበለውም አትሰበስብም፤ይህም ፍሬ ግብር የሚባለው በለም ፤ በለም ጠፍ ፤ በጠፍ ተብሎ በሦስት ደረጃ ተከፋፍሎ በገንዘብ እንዲከፈል መንግሥት ዓዋጅ ባወጣ ጊዜ ፤ በለም ለአንድ ጋሻ የኢት ፲፰ ፤ ብር በለም ጠፍ ፲ ብር በጠፍ ፤ ፰ ብር ስለሆነ በዓመት በዚህ ዋጋ ዓመቱን ሙሉ በቅስና ፤ በድቁና ፤ በድብትርናና በሌላውም መደብ ቢሆን ካህናትን ደልድሎ ማስገልገል በፍጹም የማይቻልና አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ቤተክርስቲያን ማንኛውም የሰሞን ጋሻ መሬት የያዘ ሁሉ ካህን ከሆነ እንደቀድሞው ሥሪት ራሱ በግንባር እያገለገለ የፍሬ ግብሩን ሒሳብ እንዲያካክስ ፤ ካህን ካልሆነና ካህንም ሆኖ በግንባር ማገልገል ካልቻለ ፤ በርሱ ቦታ ተተክቶ አገልግሎቱን የሚፈጽምለት ካህን ራሱ ቀጥሮ ደመወዙን እንዲከፍል ስለተደረገ ፤ በፍሬ ግብር በኩል በቀጥታ አገልጋይና አስገልጋይ ተስማምተው ፤ ለያንዳንዱ ቤተክርስቲያን መገልገያ ካልሆነ በስተቀር ወደቤተክህነት የሚገባ ገንዘብ የለም ።

እንግዲህ ቤተክርስቲያን ከጎጃም ፤ ከበጌምድርና ሰሜን፤ እንዲሁም ከኤርትራ ጠ/ግ/ በስተቀር በሌሎች ጠ/ግ/ ውስጥ ካሉት የሰሞን መሬቶች ልታገኘው የሚገባት ገቢ በድምር እንደሚከተለው ተመልክቷል ፤ ከርሻ ጥቅም ግብር በጊዜው መሠረተ ግምት የዓመቱ ገቢ የኢት $2.192.242 /ሁለት ሚሊዮን፤አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሁለት ብር/ ሲሆን ፤ ከዚሁ ውስጥ በከፍተኛ ግምት ይገባል ተብሎ የሚታመ



www.ethiopianorthodox.org

ንበት ፤ የኢት $400.000 /አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሽህ ብር ነው ። ከትምህርት ገቢ ደግሞ የዓመቱ ገቢ መሠረተ ግምት የኢት $599.907 አምስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሽህ ሁለት መቶ ሰባት ብር/ ሲሆን ፤ በከፍተኛ ግምት ይገባል ተብሎ የሚታመንበት የኢት $400.000 አራት መቶ ሽህ ብር/ ነው ።

ይህ ከትምህርት ግብር የሚገኘው ገቢ በመላ ኢትዮጵያ ተበታትነው በየቤተክርስቲያኑ ለሚገኙት ጥንታውያን ትምህርት ቤቶችና በየሀገረ ስብከቱ ለተቋቋሙ የቤተክርስቲያን ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች መምህራን ደመወዝ እጅግ አነስተኛ በሆነ መጠን ተደልድሎ የሚከፈል ነው ። በዚህ ዓይነት ደመወዝ እየተከፈላቸው የሚሠሩ መምህራን ቊጥር ከአንድ ሽህ በላይ ይሆናሉ ።

ከእርሻ ጥቅም ግብር ይገባል ተብሎ የሚገመተው ገንዘብ ደግሞ ለአገልግሎታቸው የሚሆን መሬት ላላገኙ ፤ መተዳደሪያ መሬት ቢኖርም መሬቱ በሌላ ሰው እጅ በመሆኑ ምንም ጥቅም ለማያገኙና ፤ መሬት ቢኖራቸውም ራሳቸው ፤ አርሰው በቂ ጥቅም ሊያገኙ ላልቻሉ ካህናት የወርና የዓመት ደመወዝ ፤ ከጎጃም ፤ ከጎንደርና ስሜን እንዲሁም ከኤርትራ ጠቅላይ ግዛቶች በስተቀር ለሌሎቹ በአሥራ አንዱ ጠቅላይ ግዛቶች ፤ ውስጥ በየወረዳው ፤ በየአውራጃውና በየጠቅላይ ግዛቱ እንዲሁም በዋናው የቤተክህነት ጠቅላይ ፤ ጽ/ቤት የሚገኙ ሰባክያን ፤ መምህራንና ሠራተኞች ደመወዝና ፤ ሥራ ማስኬጃ በጠቅላላም ቤተ ክርስቲያን ገቢዋ አነስተኛ ቢሆንና አቅሟም ባይፈቅድ ላለባት ማናቸውም ዓይነት ግዴታ ማስፈጸሚያ እንዲውል ቤተ ክህነቱ ከቤት ኪራይ በዓመት ከሚያገኘው ሦስት መቶ ሽህ ብር ጋር በየዓመቱ እየተደለደለ ይሠራበታል ። በዚህ መልክ የሚከፈላቸው ካህናት ፤ ሰባክያን ፤ መምህራንና ሠራተኞች ቊጥራቸው እጅግ ከፍ ያለ ሆኖ ይታያል ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግዴታዋና ኃላፊነትዋ እንደጊዜው ሁኔታ እየከበደና እያደገ እንደመሄዱ መጠን ገቢዋም እንዲሁ ከፍ እያለ መራመድ ሲገባው የነበረውን እንኳ አግኝታ ለመሥራት የምትችልበት ዕድል ስላላገኘች በከፍተኛ ችግር ላይ ትገኛለች ። ይኸውም ፤

ሀ/ በገቢዋ የምትተዳደር ስለሆነች የራሷን ገቢ ራሷ በመሰብሰብ በዚህ ዓይነት ትሠራ የነበረው ቀርቶ ገንዘብ ሚኒስቴር የሚመጣለትን የቤተክርስቲያን ገቢ ፤ እየሰበበ የሰበሰበውን ብቻ እንዲሰጣት በመደረጉና ገንዘብ ሚኒስቴርም የገቢውን ሒሳብ ራሱ ነዞ ገንዘቡ በተሰበሰበ ጊዜ ራሱ በሚያምንበት ብቻ የሚከፍል በመሆኑ ፤

ለ/ የገቢ ጥቅም ግብር ዓዋጅ ከመሬት የሚገኘውን የእርሻ ጥቅም ግብር በሠንጠረዥ «ለ» እና ሠንጠ ረዥ «መ» በሚል በሁለት የከፈለው ስለሆነ ፤ በሠንጠረዥ ለ» የተመለከተውን ገቢ ቤተክርስቲያን ከሰሞን መሬቷ ልታገኘው አይገባትም በማት እስካሁን ስትቀበል የቆየውን ገቢ ገንዘብ ሚኒስቴር በመቀነሱና ከ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ምሮ የተቀበለችውንም እንድትመልስ በማለቱ ይገባል ተብሎ የተገመተውንም ቤተክርስቲያን ፤ ልታገኝ ባለመቻሏ አቤቱታዋን ፤ በየጊዜው አቅርባ ውጤቱን በመጠባበቅ ትገኛለች ። በዚህ ዓይነት በአነስተኛ ግምት ይገኛል የተባለው ያው $1.400.000 እንኳ ሊገባ የማይችል ሆኗል ።

፫ኛ/ ከላይ እንደተገለጸው የቤተክርስቲያን አስተዳደር ራሳቸውን ችለው በሚተዳደሩ ገዳማትና አድባራት የተከፋፈለ ስለሆነ ገዳማቱም ሆኑ አድባራቱ ንብረታቸውንና ዘባቸውን በጠቅላላው ፤ ሀብታቸውን ይዘው ጠብቀው አልምተው የተቋቋሙባቸውን መንፈሳውያን ተግባሮችና ዓላማዎች አስፋፍተው በመፈጸም የሚሠሩ ናቸው ። በእንደዚህ ያለ አስተዳደር ተቋቁመው የሚሠሩ ጥንታውያንና በቅርቡም የተቋቋሙ ገዳማት ገራችን በብዛት ይገኛሉ ።



፬ኛ/ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በአቋሟ ብቻ ሳይሆን በሥራዋ ሁሉ የመንግሥቱና የሕዝቡ በመሆኗ ፤ በቅርቡ በሀገሪቱ በአንዳንድ ክፍሎች በደረሰው ድርቅ ምክንያት የደረሰውን ችግር ለመቋቋም የተቻላትን ከማድረግ አልተቆጠበችም ። በሀገራችን ከፍተኛዋ ፤ የምግባረ ሠናይ ድርጅት ሆና ፤ የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንእንደ መሆንዋ ፤ ችግረኞች ፤ ሕመምተኞችና ደካሞች የሆኑ ሁሉ መጠጊያና ርዳታ ለማግኘት የሚመጡት ወደቅጽረ ቤተክርስቲያን ነው ። ስለዚህ ርዳታ ፈላጊውና ርዳታ አቅራቢው የሚገናኙበት ፤ ቤተክርስቲያን ስለሆነች ፤ የሙት ልጆች አካላቸው የጎደለና ጠዋሪ ቀባሪ ያጡ ደካሞች ሁሉ በእምነትና በተስፋ ወደቤተክርስቲያን ፤ ይመጣሉ ።

በቅርቡ ፤ በወሎ ፤ በትግሬና በሰሜን ሸዋ እንዲሁም በአንዳንድ ሥፍራዎች በደረሰው ችግር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን በየሰበካ ቤተክርስቲያንናቸው በግልም ሆነ በኅብረት ለችግረኞቹ የሚገባውን ርዳታ በበሰለ እሕልም ሆነ በልብስና በገንዘብ ፤ በጉልበትም በተቻላቸው መርዳታቸውን አላቋረጡም ። በካህናትና በመምሕራን የማይቋረጥ መንፈሳዊ ምክርና ትምህርት ፤ ምእመናን በክርስቲያናዊ ስሜት በግልና በኅብረት በየሠፈራቸውና በየመሥሪያ ቤታቸው ገንዘብ እያዋጡ የፈጸሙት በጎ አድራጎት ፤ ሁሉ ከሃይማኖታቸው ጋር የተያያዘ መሆኑ አይካድም ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባቋቋመችው የአብያተ ክርስቲያናት ተራድኦ ድርጅት አማካይነት የደረሰውን ችግር በመግለጽ ርዳታ እንዲደረግ ጀኔብ ለሚገኘው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አስቸኳይ መልእክት በቅድሚያ አስተላለፉ ችግር ወደ ደረሰባቸው ግዛቶች መልእክተኞችን በመላክ የተጣራውን ሁኔታ አከታትሎ ለማኅበሩ ጽ'ቤት በማስተላለፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ርዳታ እንዲደርስ ማድረጓ የሚታወስ ነው ። ይህን በመሰለው ብሔራዊ ችግር በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት ፤ ቤተክርስቲያንና ሕዝቡ አንድ ሆነው ተባብረው መሥራት ከጥንት ሲያያዝ የመጣ መሠረታዊ ባሕላችን ስለሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህ ከጀኔብ የዓለም አብያተ ክርስቲያን ማኅበር ጠይቃ ያገኘችውከ$1C0 000 በላይ የሆነ ገንዘብ እንደደረሳት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች ቤተ ክርስቲያን ጭምር ለምትገኝበት ጉባኤ በማስረከብ አስፈላጊው ርዳታ ወዲያው ለችግረኞቹ እንዲደርስ አድርጋለች ። በዕርዳታውም ማከፋፈል ተግባር ላይ ካህናት በሙሉ በመተባበር ተካፋይ ሆነዋል ።

ይህ የደረሰው ችግር ከባድ እንደመሆኑ የቤተ ክርስቲያን የርዳታ ተካፋይነት በዚህ ብቻ ሊወሰን የማይገባ መሆኑን በመመልከት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገኘውን ማናቸውንም ርዳታ በማስተባበር አስፈላጊውን የሚፈጽም አንድ የተለየ ጉባኤ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ተሠይሞ ፤ በከፍተኛ ደረጃ ያሉትን አባሎች ጭምር ወደ ሥፍራውም ድረስ በመላክና በቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት ውርጥ ራሱን የቻለ የምግባረ ሠናይና ማኅበራዊ አገልግሎት ክፍል በማቋቋም የርዳታ ሥራው ይካሄዳል ። በዚህም መሠረት አስፈላጊውን ዝግጅት በማሟላት በአሁኑ ጊዜ እናት አባት የሞተባቸውን ሃያ አራት ወንዶችና ሃያ ስድስት ሴቶች በድምሩ አምሳ ሕፃናት ከወሎ ሀገረ ስብከት በማስመጣት ቤተ ክርስቲያን ተገቢ ውን ርዳታ በማበርከት ላይ ስትሆን ፤ ይኸውም ርዳታ በእነዚህ ሃምሳ ሕፃናት ብቻ ሳይወሰን ወደፊት የሚቀጥል መሆኑ ታውቋል ።

በዚህ ረገድ ለተጀመረው በጎ ሥራ የሚያስፈልገውን ወጭ በተቻለ መጠን ለማሟላት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በቅድሚያ ከተገኘው በቀር ከቤተ ክህነት ሂሳብና ከዚያው አነስተኛ ከሆነው ከጠቅላላው የቤተ ክህነት ሠራተኞች ከወር ደመወዛቸው ከመቶ አሥር በመክፈል፤እንዲሁም ከየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ሙዳየ ምፅዋት ከወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበሮችና ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች የኢት $50-000 ያህል ተሰብስቦ ገቢ መሆኑ ተነግሯል ።

ተከታዩን በ፴፫ኛው ገጽ ይመልከቱ




www.ethiopianorthodox.org

# የዓመቱ ዋና ዋና መንፈሳዊ ነክ ዜናዎች

## ግ ብ ፅ

በግብፅና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ከጥንት ጀምሮ ጸንቶ በኖረው አንድነትና ወዳጅነት መሠረት ብፁዕ ወቅዱስ ሣልሳዊ ሲኖዳ የእስክንድርያ ፓፓና የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በተደረገላቸው የክብር ጥሪ መሠረት መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለ፰ ቀናት ያህል ጉብኝት አድርገዋል ።



ብፁዕ ወቅዱስ ሣልሳዊ ሲኖዳ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጋር የደብረ ሊባኖስን ገዳም ሲጎበኙ

በዚህም ጊዜ ቅዱስነታቸው በኢትዮጵያ የሚገኙትን ታሪካዊ ቦታዎችን ከመጎብኘታቸውም በላይ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጋር ስለ ሁለቱ እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት የወደፊት ግንኙና እርምጃ በሰፊው ተወያይተዋል ።

## ቆ ጵ ሮ ስ

ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት መቃርዮስ የቆጵሮስ ፕሬዚዳንት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ባደረጉላቸው የክብርና የወዳጅነት ጥሪ መሠረት ከጥቅትም ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ጀምሮ ለአምስት ቀናት ያህል ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል ።

ተከታዩን በ፴፰ኛው ገጽ ይመልከቱ



፰ኛ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከላይ ባጭሩ እንደተገለጸው በገቢዋ ማነስና ይህም እያደር እየቀነሰ ሲሄድ በዚህ አንጻር ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት እየጨመረ በመሄዱ ፤ የአገልጋዮች ብዛትና ከአገልግሎታቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አበል ለመክፈል ባለመቻሉ ፤ ቤተክርስቲያን ያለባትን የወደፊት ግዴታ በመመልከት ቤተክርስቲያን በቅርቡ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነ አንድ ታላቅ የሥራ ምዕራፍ ከፍ ታለች ። ይኸውም ስለ ቤተክርስቲያን የሰበካ አስተዳደር በቃለ ዐዋዲ ያወጣቸው ያስተዳደር ሕግና ሕጉ በሥራ ላይ እንዲውል የምታደርገው ከፍተኛ ጥረት ነው ።

በዚህ የሰበካ አስተዳደር ደንብ መሠረት እያንዳንዱ ሰበካ ቤተክርስቲያን በሀገረ ስብከቱ ሥር ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ እንዲሠራ ፤ በሰበካው ክልል ውስጥ የሚገኙት ካህናት እና ምእመናን ሴቶችም ወንዶችም ሁሉ ተመዝግበው የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባሎች የሚሆኑትን በመምረጥና ራሳቸውም በአባልነት በመመረጥ ሙሉ የሥራና የሥልጣን ተካፋዮች እንዲሆኑ ተደርጓል ። ከዚህም በቀር የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ማናቸውም ዓይነት ሀብት ፤ ንብረትና ገቢ ምእመናኑ በአሥራት መልክ በፈቃዳቸው ለዚያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ከሚከፍሉት የአስተዋጽኦ ገንዘብ ጋር በአንድ ነት ሆኖ ይኸው ገንዘብና ንብረት ራሳቸው በመረጧቸው የአስተዳደር ጉባኤ አባሎች በሆኑት ካህናትና ምእመናን ሥልጣን ለካህናትና ለሌሎቹ ሠራተኞች ደመወዝ ፤ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማስፈጸሚያ ፤ ለትምህርት ቤት ማቋቋሚያ ፤ ለስብከተ ወንጌል ማስፋፊያና ለችግረኞች መረጃ እንዲውል ተፈቅዷል፤ ካህናትና ምእመናን በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ብቻ ሳይወሰኑ በየጊዜው በየአውራጃውና በየጠቅላይ ግዛቱ በመጨረሻው በዓመት አንድ ጊዜ አዲስ አበባ በመንበረ ፓትርያርኩ በሚደረገው የቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከየአንዳንዱ ሰበካ የተውጣጡ ካህናትና ምእመናን በሙሉ አባልነት ተካፋዮች እንዲሆኑ በማድረግ በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትና ምግባረ ሠናይ ፤ ትምህርትና ስብከት ፤ አስተዳደርና በመሳሰሉትም ዝርዝር ጉዳዮች ተነጋግረው እንዲወሰኑ ይኸው የሰበካ አስተዳደር ደንብ የሚያረጋግጥ ስለሆነ በዚህ ካህናትና ምእመናን ሙሉ ተካፋዮች በሆኑበት አሠራር ዛሬ ያለውን የቤተክርስቲያን ችግር አስወግዶ ለወደፊቱ የሥራ እርምጃ የሚያስተማምን መሠረት እንደሚሆን ታምኖበታል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዛሬና ወደፊት የሚጠብቃት ኃላፊነትና ግዴታ በቀላሉ የሚገመት ባለመሆኑ ታሪካዊና ጥንታዊ የሆነ ክብርንና መብትን በመጥቀስ ብቻ ልትኖር አይገባትም ።

የሲሶ መንግሥት ታሪካዊ ስጦታ ከሰሞን መሬት ይገኛል ተብሎ በመንግሥት እየተሰበሰበ የሚሰጣት ገቢ ገንዘብ ድርሻዋና የአሰባሰቡ ሁኔታ ፤ ለመገልገያና ለመተዳደሪያ የተሰጧት የሰሞን መሬቶች ይዞታና ሥሪት ፤ የገዳማት ፤ የአድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ሁኔታ እንደገና እየተመረመረ ለዘመኑ የሚስማማውንና ቤተ ክርስቲያን ራሷን የምትችልበትን ተገቢውን ውጤት ማግኘት በብርቱ የሚያስፈልግ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ ፒሜን የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

በዚህ ጊዜ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጋር ስለ አብያተ ክርስቲያናት አንድነትና ተግብሮ መሥራት ሰፋ ያለ ውይይት አድርገዋል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት መቃርዮስ ጋር ስለ ጥንታውያን የኢትዮጵያ መጻሕፍት ሲወያዩ ።

# መስኮብ

ፓትርያርክ ፒሜን የመስኮብና የመላው ሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባደረጉላቸው የክብር ጥሪ መሠረት ከጥር ፱ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ጀምሮ ኢትዮጵያን ለአንድ ሳምንት ያህል በኦፊሴል ጐብኝተዋል ።

በዚሁ ወቅት ቅዱስነታቸው ታላላቅ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ገዳማትንና አድባራትን፡ከመ ጐብኘታቸውም በላይ በንጉሠ ነገሥቱ መናገሻ በአዲስ አበባ ከተማ በጃንሆይ ሜዳ በተደረገው የበዓለ ጥምቀት የጸሎት ሥነ ሥርዓት ተካፋይ ሆነዋል ።

እንዲሁም አሁንም ሆነ ለወደፊቱ በሩሲያ ስለሚማሩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ለወደፊቱ ስለሚፈጽሟቸው ሥራዎች፣ ይህ ጸንቶ የኖረው የወዳጅነት መንፈስ ይበልጥ ስለሚጠነክርበት፣ መንፈሳዊው አገልግሎት ከአሁኑ በበለጠ ለምዕመናን ስለሚደረስበት ጉዳይና ስለ መሳሰሉትም ፓትሪያርክ ፒሜን ከብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጋር ሰፋ ያለ ውይይት አድርገዋል ።

በተጨማሪም ፓትሪያርክ ፒሜን በድርቅ ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ይሆን ይሆን ዘንድ $ 10.350 ብር ለግሠዋል ።

ሣህለ ድንግል ሰብስቤ



www.ethiopianorthodox.org

# ክቡር አቶ መኰንን ዘውዴ

## አዲሱን ሥራቸውን ጀመሩ

ክቡር አቶ መኰንን ዘውዴ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድ ሚያዝያ 8 ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ ም የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሆነው መሾማቸው የሚታወስ ነው ።

ክቡርነታቸው ይህንኑ አዲሱን ሥራቸውን ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ሲጀምሩ በመንበረ ፓትርያርኩ አዳራሽ ተገኝተው ስለ ወደፊቱ የሥራ መመሪያቸው ለሠራተኞቹ አንዳንድ ገለጻ አድርገዋል ። በዚህን ጊዜ ሥራውን የሚያከናውኑት በጠቅላላው ከሠራተኛው ጋር መሆን በማውሳት የሠራተኛውን ትብብርና ቅን አስተሳሰብ እንዳይለያቸው ከአደራ ጋር ጠይቀዋል ።



ክቡር አቶ መኰንን ዘውዴ

ክቡርነታቸው ወደፊት ስለሚፈጽሟቸው ሥራዎች ከስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ መምሪያ ተጠይቀው የሰጡት መልስ ከዚህ የሚከተለው ነው ።



፩ኛ ጥያቄ ፤ ክብር አቶ መኰንን ዘውዴ የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፤ ክቡርነትዎ የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሆነው በመሾም እነሆ ሥራውን ጀምረዋል ፤ ለወደፊቱ ስለ ቤተ ክህነት አስተዳደር ያለዎት እቅድ ምንድነው ?

መልስ ፤ አስቀድሞ ትንቢት ለመናገር የነቢይነት እድል ከተሰጣቸው ሰዎች በስተቀር የወደፊቱን መተንበይ አይቻልም ፤ ይህን አደርጋለሁ (እሠራለሁ) ማለትም፤ሳይሠሩ መናገር ይሆናል ፤ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ሥራ በዘመናዊ እቅድ ለመምራት ያለኝ አሳብ በኔ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አባሎችና ደጋፊዎች ጭምር የሚፈጸም ነው ፤ ስለዚህም ከቤተ ክህነት አንድ አጠቃላይ መግለጫ ስለተሰጠ ፤ ነጥቦቹ ከዚያው ላይ ተጠቅሰዋል ፤ በነዚያ መሠረትነት ሥራው ሊካሄድ ይችላል ። ከዚህም በስተቀር የሥራ አስኪያጁን ሥራ በቅርብ ሆነው የሚያዩና ፤ ችግሩን የሚያቃልሉ ፲፪ አባሎች የሚገኙበት የቤተ ክህነት ጉባኤ የተቋቋመ ስለሆነ የአባሎቹ ስም ይገለጣል። ስለዚህ እኔም በሐሳቤ ያለውን ጥናት ካጠናቀቅሁ በኋላ ማናቸውም ሐሳብ ለጉባኤው ቀርቦ ፤ ወደፊት ሥራውን በተቻለ መጠን ለማቃናትና ለመምራት የእግዚብሔርን ፈቃድና ርዳታ በመጠየቅ ሙሉ ተስፋና ፈቃድ አለኝ ።

፪ኛ ጥያቄ ፤ ከሁሉ አስቀድሞ ሊፈጸም ይገባዋል ብለው የሚያምኑበት የሥራ ዓይነት የትኛው ነው ?

መልስ ፤ በእውነቱ ይህ ይቀድማል፤ይህ ይከተላል፤ የሚባል ሳይሆን ሁሉም ጐን ለጐን ሊራመድ የሚገባው ነው ፤ ተራ የሚሰጠው የተሠራ ነገር ሲኖርና ሲታይ ነው፤ አሁን እንደማየው፤ሁሉም መሠራትና ሊሠራ የሚገባው እንጂ ይህ ይሻላልና ከዚህ ይህን ላስቀድም የሚባል አይደለም ፤ እርግጥ ነው ከሥራው ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸው አሉ። ለምሳሌ ለቤተ ክርስቲያን የደም ሥር የሆነው ስብከትና ትምህርት ፤ ይህን የመሳሰለው ሁሉ በተቻለ መጠን ከሁሉ በፊት ቅድሚያ መስጠት ያስፈልገዋል ፤ ስለዚህ አሁን ኃይላችንን ልናጠነክር የሚገባን ከዚሁ ላይ ነው ፤ ደግሞ ሥራ ሁሉ የሚከናወነው በገንዘብ ስለሆነ፣በገንዘብ አሰባሰብና አያያዝ በኩል ያለውንም በተቻለን መጠን ለማፋጠን ከፍ ያለ ሙከራና ጥረት ማድረግ ይኖርብናል ።

፫ኛ ጥያቄ ፤ የኢትዮጵያ ድርሻ የሆነው ገንዘብ ፤ በገንዘብ ሚኒስቴር እጅ ገብቶ አልወጣ ስለአለ ካህናት የበይ ተመልካች ሆነዋል እየተባለ ይነገራል ይህ እውነት ነውን ? እውነትስ ከሆነ ክቡርነትዎ የቤተ ክርስቲያንን ሀብት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የገንዘብ ሚኒስቴር እንዴት ሊያላቅቅ ይችላል ?

መልስ ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ፤ ሰብሳቢ ሆኖ ቤተ ክህነትን ረዳ እላለሁ እንጂ በእውነቱ ገንዘቧን ከለከለ አልልም ፤ ችግሩ የመቆጣጠሩና የመከታተሉ ጉዳይ ነው፤ምክንያቱም የሰሞን መሬቶችን ዳር ድንበራቸውንና ልካቸውን አውቆ ይህን ያህል ነው ያለን ይህን ያህል ቀርቶናል ማለቱ የባለ ንብረቱ ፋንታ ሊሆን ይገባል ፣ እንዲያው ዝም ብሎ ቍጥጥር ሳይደረግ በተጨማሪ በሥራው ላይ ደርቦ የሚሠራውን መሥሪያ ቤት ይህን አደረገ ማለቱ በውነቱ የማላምንበትና የማልስማማበት ነገር ነው ። ለወደፊቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ጋር እየተነጋገርሁ አስፈላጊው ነገር እንዲፈጸም ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት አደርጋለሁ ።

፬ኛ ጥያቄ ፤ ቃለ አዋዲ የሚባል የሰበካ ጉባኤ ደንብ ወጥቶ በየሀገረ ስብከቱ ተላልፏል ክቡርነትዎ ደንቡን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ያለዎት ፈቃድና ስሜት ምን ያህል ነው ?



www.ethiopianorthodox.org

መልስ ፤ በቃለ አዋዲ የተመለከተው የሰበካ ጉባኤ የሥራ ፕሮግራም ፤ ዝርዝሩ በጣም ሰፋ ያለ ነው ፤ ብዙ ድርጅት ብዙ ሠራተኛም የሚጠይቅ ነው ፤ አንድን ነገር አስቀድሞ በስፋት የሚደረገውን ከመናገር ይልቅ የሚያቀናብረውን ክፍል ማጠንከርና ማቋቋም ያስፈልጋል ፤ አሁን እንዳየሁት ሕጉ ሰፊ ነው ፤ ነገር ግን ሥራውን የሚያስፈጽመው ክፍል በጣም ጠብቦ ነው ያየሁት ፤ እርግጥ ተግባሩ አስፈላጊና የሚያደገፍ ፤ ማንም ሰው ሊተባበርበት የሚገባ ነው ፤ ስለዚህ አሁን የተባለውን ክፍል በማሟላትና ጉዳዩን በጥብቅ የሚከታተሉ ሠራተኞችን በማዘጋጀት ፤ የጐደለውን በማሟላት፤ ለማጠንከርና የበለጠ ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ በሥራችን ቅድሚያ ተሰጥቶት የምናስብበት ሆኗል።

ጥያቄ ፤ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላት ግንኙነት በምን አቅጣጫ ሊሆን ይገባል ይላሉ ?

መልስ ፤ ቤተ ክርስቲያንን ከውጭ ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት ከሁሉም በበለጠ ሊታሰብበት የሚገባ ነው ፤ ምክንያቱም የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ርዳታ ለማድረግ ያላቸው ፈቃድ ፤ ካሁን በፊት ራሴ ተረድቸዋለሁ ፤ አሁንም በብዙ ነገር እጃቸውን ከመዘርጋት አልተቆጠቡም ፤ ነገር ግን ከብዙ ሥፍራ ርዳታ ከመጠየቅ በፊት ሙሉ ዝግጅትና አቋም እንዲኖራው ያስፈልጋል፤ ዝም ብሎ ርዳታ በመጠየቅ የመጣውን ከአልሆነ ቦታ ማዋል ደግሞ ፤ የበለጠ አገርን የሚያስነቅፍ ፤ የሚያስድብና እምነትን የሚያሳጣ ነው ። ደግሞም እኛ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የምንሠራው ሥራ ሁሉ በማንም ዘንድ እምነት ሊኖረን የሚገባ ስለሆነ አስቀድሞ የምንጠይቃቸውን ርዳታዎችና የግቡን ዓላማ ማወቅ አለብን ፤ ከዚህ በኋላ ግን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነታችንን በበለጠ እያስፋፋን፤ከዚያም በኩል እየተረዳንና ሥራችንንም እያሳየን ለመሥራት ፤ ራሱን ችሎ የሚከታተል አንድ መምሪያ መኖር ስለሚያስፈልገው ይህ በጥናታችን ውስጥ ያለ ነው፤ሲሉ ክቡር ሥራ አስኪያጁ በጠቅላላው ለወደፊት ስለ ቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ዓላማ ገልጸዋል ።



# በድርቅ ምክንያት ለተጐዱት ወገኖች ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ርዳታ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሕዝብ የማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ በተቀዳሚነት እየገባች የኃዘኑና የደስታው ተካፋይ በመሆን ርዳታዋን ስታቀርብ ኑራለች፤ ወደፊትም ትኖራለች ።

ቤተ ክርስቲያን በተለይ የርኁባን ጉርስ ፤ የዕሩቃን ልብስ ፤ የድሀ አደጎች ማሳደጊያ፤ የሽማግሌዎች መጠጊያ፤ የበሽተኞች መጠለያ፤የድኩማን መረጃ በጠቅላላው የበጎ አድራጎት ምንጭ ኾና በመኖርዋ«የድሆች እናት»የሚል የቅጽል ስም ተሰጥቷታል ።

የማይደኸይ፤ የማይሾምና የማይሻር እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን፤የሰው ልጅ ግን በልዩ ልዩ ምክንያት የከበረ የሚከብርና የሚደኸይ፤ የሚሾምና የሚሻር መሆኑን ጤንነቱንም ሆነ ሀብቱን፤ክብሩንም ጭምር፤በልዩ ልዩ ምክንያት የሚያጣ መሆኑን፤ በመረዳት የሰው ልጆች ማኅበራዊ ኑሮ እንዲጠነክር፤ ምግባር ትሩፋትን እያስተማረች ችግርተኞች እንዲረዱ ስታደርግ ኖራለች ።

ሕዝቡም በትምህርቱ መሠረት ያለው ለሌለው ሲሰጥ ማለት ቀዶ ሲያለብስ፤ ቆርሶ ሲያጎርስቆይቷል።በተጨማሪም የሙት ልጆችን ወስዶ በማሳደግ ጧሪ፤ቀባሪ የሌላቸውን ድኩማን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ በመቃብር ቤት አስቀምጦ የልብስና የጉርስ ስጦታ ለማድረግ እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ ሲረዳ ቆይቷል ።

ጥንትም ሆነ አሁን ይህ የበጎ አድራጎትና የምጽዋት አሰጣጥ ሥርዓት በሕዝቡ ዘንድ ያልተጓደለና ገንዘቡም ያላረፈ ቢሆንም «ቀኝህ የሚሠራውን ግራህ አይወቅ» በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችውንና የምታደርገውን የበጎ አድራጎት ሥራዋን ካለ እግዚአብሔር በቀር የሚያውቅላት የለም ።

በአሁኑ ጊዜም በሀገራችን በድርቅ ምክንያት በገባው ረሀብና በሽታ ለሚሠቃዩት ወገኖች የገንዘብ ርዳታ ከማድረጓም በላይ በረሀብና በህመም አባት እናታቸውን ያጡትን የሙት ልጆች አስመጥታ በማሳደግ ላይ ትገኛለች ።

ቤተ ክርስቲያን ከማናቸውም ክ ፍል አስቀድማ በሀገር ውስጥ የደረሰውን ችግር በማስረዳት ርዳታ እንዲሰጣት ጥያቄዋን ጀኔቭ ለሚገኘው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በማስተላለፍ የተላከላትን ከ$100.000ብር በላይ የሆነ የገንዘብ ርዳታ ሰብሳቢ ኮሚቴ ሰጥታለች ።

እንዲሁም ከመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ጀምሮ(አንሥቶ) በየሀገረ ስብከቱ ከሚገኙት የቤተ ክህነት ሠራተኞች ከወር ደመወዛቸው ላይ በመቶ አሥር ሂሳብ ተቀንሶ አስተዋፅዖ ተደርጓል ።

በመላው ኢትዮጵያ ከሚገኙት (ካሉት) አብያተ ክርስቲያናት የሦስት ወር ሙዳየ ምፅዋት ተሰብስቦ ለዚሁ ችግር መርጃ እንዲውል ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ገዳማትና አድባራት የተለየ አስተዋፅዖእንዲያደርጉ የተሰጠው ውሳኔ በሥራ ላይ ውሎ ከላይ ከተዘረዘሩት ምንጮች የሚገኘው የርዳታው ገንዘብ እየተሰበሰበ ባንክ በተከፈተው ሂሳብ ውስጥ ገቢ በመደረግ ላይ ይገኛል ።



www.ethiopianorthodox.org

እስከ አሁን በተደረገው የርዳታ አሰባሰብ ተግባር ፤

ከቤተክህነት ድርሻ $ 10.000

» » ከዋና መሥሪያ ቤት ሠራተኞች መዋጮ $ 70-360

ከልዩ ልዩ መዳዬ ምጽዋት $ 2000

ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር $ 103-500

ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ፒሜን የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ ፓትርያርክ $ 3.000

በድምር $ 138.850

የተገኘ ሲሆን የርዳታው ገንዘብ አሰባሰብ በመቀጠል ላይ ነው።እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር የተቋቋሙት የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራትየጥሬ ገንዘብና የልብስ ርዳታ ያደረጉ ሲሆን ለወደፊቱም ርዳታው የሚቀጥል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ።


ጌታቸው አበራ



# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምግባረ ሠናይ ድርጅት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቋምና ዓላማ የወንጌልን ትምህርት ላልደረሰበት ማዳረስ ብቻ ሳይሆን «ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው» ። የሚለውን መለኮታዊ ቃል መሠረት በማድረግ ለተቸገሩት ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን በተቻለ መጠን ትረዳለች ። በተለይም ባሁኑ ጊዜ የተቀደሰ ዓላማዋን ለተከተዮችዋ በጉልህ ሠርታ ለማሳየት የምታደርገው ጥረት ከመቸውም ይልቅ የሚያስደስት ሆኖአል ።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቀው ሁሉ በሀገራችን ድርቅ ካጠቃቸው ጠ/ግዛቶች አንዱ ወሎ መሆኑ ይታመናል።በወሎ የሞተውና በችግር ላይ ያለው ሕዝብ በቊጥር ከፍ ብሎ ሲወራ እንሰማለን ። ሆኖም ባሁኑ ጊዜ ደግሞ ከውጭ አገርም ሆነ ከውስጥ በሚደረገው ርዳታ ሕዝቡ ከችግር ለማምለጥ በመንሰራራት ላይ መሆኑን የዓይን ምስክሮች ይናገራሉ ። በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ለሚገኙ ወገኖቻችን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች በጎ አድራጊዎች ጋር በመተባበር የሚፈለግባትን ግዴታ ካሁን በፊት በተቻለ ፍጥነት $105,000 በመልካም ልግሥና ቀዳሚ ሆና የሰጠች ለመሆንዋ በሬዲዮም፤ በጋዜጣም ሲነገር የሰማው ሁሉ ያምንበታል ።



የኢትዮጵያ ቤተ፡ክርስቲያን ከድርቅ ቀበሌ አስመጥታ ከምትረዳቸው ወንዶች ልጆች መካከል ጥቂቶቹ

በዚህ ብቻ መወሰን እንደማይገባት በመገንዘብ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ አዲስ አበባ በሚገ




www.ethiopianorthodox.org

ኘው ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ፤አባት እናት ለሞቱባቸው ሕፃናት ማሳደጊያ አንድ ድርጅት እንዲቋቋም አድርገዋል ። ይህ ድርጅት በመንበረ ፓትርያርኩ ጠ/ጽ/ቤት ሥር የሚተዳደር ሆኖ «ምግባረ ሠናይና ማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት» ተብሎ እንዲጠራ ተወስኖአል ።

ለድርጅቱ ኮሚቴ ተመርጦለት በጀት ተመድቦለት ፤ ጽ/ቤት ተቋቁሞለት ፤ ቦታም ተከልሎለት በጥሩ ሁኔታ ከተዘጋጀ በኋላ በችግር ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ አምሳ ሕፃናት ከወሎ ጠ/ግዛት አስመጥቶ በማሳደግ ላይ መሆኑ ተረጋግጦአል ።

ካንድ ወር በፊት በኢ.ት/ ቤተ ክርስቲያን ስምተወክለው ሕፃናቱን የተረከቡት የድርጅቱ ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አደመን ስለ ሕፃናቱ አመጣጥ ላደረግንላቸው መጠይቅ ሲመልሱ መንግሥት በሁለት አውራጃዎች ካዘጋጀው የችግረኞች መጠለያ የተገኙ ናቸው። ይኸውም ከአምባሰል ፳፭ ከአውሳ ፳፭ ሕፃናት ሲሆኑ እነርሱም ፳፮ ሴቶች ፳፬ ወንዶች ናቸው ብለዋል።ከዚህም በማያያዝ ስለመሠረተ ሃይማኖታቸው እንዲያስረዱን ጠይቀናቸው ሕፃናቱን ጠይቄ እንደተረዳሁት ከሆነ ሁሉም እስላሞች ናቸው በማለት ገልጸውልናል ።



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ከመታው ቀበሌ አስመጥታ ከምትረዳቸው ሴቶች ልጆች መካከል በከፊል

አቶ ብርሃኑ ስለ ሕፃናቱ አያያዝ እንዲገልጹልን ላደረግንላቸው ተጨማሪ ጥያቄ ሲመልሱ ሕፃናቱ ከመጡ ሁለተኛ ወራቸውን ይዘዋል ። ምንም እንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ አየሩ አልስማማቸው ብሎ ቢታመሙብንና ለጥቂት ቀናት ብንቸገርም ባሁኑ ጊዜ በጤንነታቸውም ሆነ በኑሮአቸው ሁሉ በጥሩ ሁኔታ ይገኛሉ ። በተለይም አሁን በሞራልና በቀለም ትምህርት ጎልምሰው እንዲያድጉ ማስፈለጉን ስለታመነበት መምህር ተቀጥሮላቸው በሚገባ ሲማሩ ይገኛሉ ። እንዲሁም ድንገተኛ በሽታ ሲይዛቸው እንዳንቸገርም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ መልካም ፈቃድ የግል ሐኪም ተቀጥሮላቸው የጤንነታቸው ሁኔታ በሚገባ ይጠበቅላቸዋል ። በሽታው የከበደባቸው እንደሆን ወዲያውኑ በድርጅቱ መኪና ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት የሕ



ፃናት ሕክምና ክፍል እየወሰድን አስፈላጊውን ሕክምና እንዲያገኙ እናደርጋለን ብለዋል ካሁን በፊት በሕክምና በኩል የረዳቸው ሌላ ሆስፒታል እንዳለ ተጠይቀው ሲያስረዱ ከሃያ በላይ የሆኑ ሕፃናት ታመውብን በጣም ተቸግረን ነበር ። ነገር ግን የልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል በመልካም ሁኔታ ተቀብሎ በሚገባ ስላከመልንና ሙሉ ጤንነት እንዲያገኙ ስለረዳን ምስጋናችን የላቀ ነው ሲሉ ሆስፒታሉን በጣም አመስግነዋል ።

ከዚህም ሌላ ስለ ምግባቸውና ስለ መኝታ ቤታቸው እንዲሁም ስለ ንጽሕናቸው ጠይቀናቸው ሲገልጹ ምግባቸውን በሰዓቱ አብስለው በማዘጋጀት የሚያቀርቡ አራት ሠራተኞች አንድ የሠራተኞች ኃላፊ በጠቅላላ አምስት ይሆናሉ ። እነርሱም በትጋትና በንቃት የሚፈለግባቸውን ግዴታ አውቀው ይሠራሉ ። ለሕፃናቱም በሚገባ ይጠነቀቁላቸዋል ። ስለ መኝታ ቤታቸው ፤ ስለ ልብሳቸውና ስለ ራሳቸው ንጽሕናም አራት ሞግዚቶች አንድ ተቆጣጣሪ በጠቅላላ አምስት አሉአቸው ። እነዚህም ልብሳቸውና ገላቸው እንዳይቆሽሽ ከመጠበቃቸውም ሌላ ሌሊት ሌሊት ብቻቸውን እንዳይሆኑ በተራ ከእነርሱ ጋር ስለሚያድሩ ችግር የላቸውም በማለት አስረድተዋል ።

እንዳየነውና እንደተረዳነውም መኖሪያ ቤታቸው በጥሩ ሁኔታና በንጽሕና ከመጠበቁም ሌላ ለያንዳንዳቸው አልጋ ያላቸው መሆኑን ለመረዳት ችለናል ። በመጨረሻም ድርጅቱ ቀዋሚ መሆኑንና አለመሆኑን መጠየቃችን አልቀረም ። ድርጅቱ እንደሚባለው ከሆነ እነዚህ ሕፃናት ሌሎች በጎ አድራጊዎች እናሳድጋለን የሚሉ ከተገኙ ለእነርሱ እየተሰጡ እነርሱን የመሳሰሉ እጓለ ማውታዎች አስመጥቶ እያሳደገ ለሀገርና ለወገን ማበርከቱን ሳይቀጥል አይቀርም ይባላል ሲሉ አቶ ብርሃኑ አደመ ገልጸውልናል ።

ገ/ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም



www.ethiopianorthodox.org

# እስላሞች ስለአደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ

ተቃውሞ ቀረበ

ባለፈው ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የእስልምና እምነት ተከታዮች የሆኑት ኢት
ባለፈው ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የእስልምና እምነት ተከታዮች የሆኑት ኢት
ዮጵያውያን የአደረጉትን ሰላማዊ ሰልፍ በመመልከት፤ሕዝበ ክርስቲያኑም ሚያዝያ ፲፬
ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ተዘጋጅቶ እንደ ነበረ የሚታወስ
ነው ።

ሕዝበ ክርስቲያኑ የተሰማውን ስሜት በሰላማዊ ሰልፍ መልክ ለመግለጽ የተነሣሣ
መኾኑን በማስታወቁ ይህ የሚደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በአስፈላጊው መንገድ እስኪ ፈጸም
ድረስ ምእመናን በአብያተ ክርስቲያናቱ ብቻ ተገኝተው ጸሎት እንዲያደርሱ በማለት
ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥያቄአቸውን ካቀ
ረቡ በኋላ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ማታ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ
እንዳይደረግ በሬዲዮና በቴሌቭዥን አሰምተው ነበር ።

በዚሁ መሠረት ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ምእመናኑ በአብያተ ክርስቲያናቱ
ተገኝተው ጸሎት ከአደረሱ በኋላ ጉዳዩ በተለይም «ኢትዮጵያ የክርስቲያንደሴት አይደ
ለችም» የሚለውና«የክርስትና ሃይማኖት ከመንግሥቱ አስተዳደር ይገለል»በማለት የእ
ስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች እጅግ በጣም ያሳሰቡዋቸው ስለሆነ
ከየአድባራቱ ምእመናንና ካህናት የተመረጡ ወኪሎች ጠቅላላ ጉዳዩ በቀላሉ ተገምቶ
እንዳይታለፍ አስፈላጊው እርምጃ ባስቸኳይ እንዲወሰድ በማለት ለብፁዕ ወቅዱስ የኢት
ዮጵያ ፓትርያርክና ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄውን አቅርበዋል ።

እነዚህ ከአብያተ ክርስቲያናት የተወከሉት ምእመናንና ካህናት ለብፁዕ ወቅዱስ
ፓትርያርኩ ጥያቄውን በአቀረቡበት ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በሰጡት መልስ ለክ
ርስቲያኖች ሁሉ መሠረቱ ትዕግሥት ስለሆነ ምንም እንኳ የሃይማኖት ጉዳይ ጊዜ የማይ
ሰጥና በቀላሉ ሊመለከቱት የማይገባ ቢሆንም ጉዳዩ ሥነ ሥርዓት በያዘ መንገድ እንዲ
ፈጸም የሚያደርጉ መሆናቸውን ገልጸው ሕዝበ ክርስቲያኑም ይህንን መንፈሳዊ ዓላማ
በመከተል ውሳኔውን በትእግሥትና በረጋ መንፈስ እንዲጠባበቁት አደራ ጭምር አሳ
ስበው ቡራኬ በመስጠት አሰናብተዋል ።

በሕዝበ ክርስቲያኑ የተወከሉት ምእመናን ለክቡር ጠ/ሚኒስትር ልጅ እንዳልካ
ቸው መኰንን ያቀረቡት አቤቱታ የሚከተለው ነው ።

ለክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኰንን
የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
ጠቅላይ ሚኒስትር
አዲስ አበባ ፤
ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሆይ !

በሀገራችን ላይ በቅርብ የደረሰውን የአስተዳደርና የፖለቲካ ሁኔታ ምክንያት በማ
ድረግ ከጥንት ጀምሮ የቆየውን የሀገራችንን ታሪካዊ አቋም ለማቃወስና በብዙ ድካም የተ
መሠረተውን አንድነታችንን ለማለያየት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሚያዝያ ፭ ቀን
፲፱፻፺፯ ዓ/ም ጽፈው ለክቡርነትዎ በአቀረቡት አቤቱታና ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም
ሰላማዊ ሰልፍ ባደረጉበትም ጊዜ በልዩ ልዩ ሰሌዳዎች ላይ ጽፈው ያቀረቧቸው ጥያቄ
ዎች እውነትን ያልተከተሉና የማይመስል ፕሮፓጋንዳ መሆናቸው ቢታወቅም በታሪኩ
ኰርቶ በእምነቱ ጸንቶ የሚኖረውንና ሰላማዊውን የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን እጅግ
አሳዝኖታል ።

የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ላቀረቡአቸው አቤቱታዎች ሆነ ለአሳዩት ሰላማዊ
ሰልፍ በአጠፌታ መመለስ የሚቻል ቢሆንም ፤ እንኳን የሀገራችንን ጸጥታ ለመጠበቅና
ሀገሪቱንም ሰላም ለማክበር ስንል ጥላቻውን በፍቅር፤ቁጣውን በትዕግሥት፤ ሐሰቱንም
በእውነት፤በመመለስና በመናገሻ ከተማችን በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተሰብስበን
ጸሎተ ምሕላ ካደረግን በኋላ በአዲስ አበባ የምንገኝ ሕዝበ ክርስቲያናት የሚከተሉትን
ጥያቄዎች ለክቡርነትዎ ስናቀርብ በተቻለ ፍጥነት ተገቢውን መልስ በቴሌቭዥን በሬ
ዲዮና በጋዜጣዎች በማሰራጨት የሕዝበ ክርስቲያኑን መንፈስ የሚያረካ መግለጫ እንዲ
ሰጥልን እንጠይቃለን ።

፩ኛ / በሀገራችን ላይ በቅርብ ጊዜ የደረሰውን የኢኮኖሚ ችግርና የአስተዳደር ሁኔታ
ምክንያት በማድረግ የካቲት ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ
ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥልጣን መረከብዎን የምንደ
ግፍ መሆናችንን እየገለጽን ፤ በሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረት ሁሉ ተባባሪነታችንን እናረ
ጋግጣለን ።

፪ኛ / ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው የዘውድ አወራረስ መሠረት ግርማዊ ንጉሠ ነገ
ሥት ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ አስፋ ወሰን በተጠባባቂ አልጋ
ወራሽነትም ሆነ በአልጋ ወራሽነት የዙፋኑ ተተኪ እንዲሆኑ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ
ያሰሙትን ብሥራት በታላቅ ደስታ ተቀብለንዋል ።

፫ኛ / ንጉሠ ነገሥቱም ሆኑ ክቡርነትዎ ሀገራችን ከደረሰባት የኢኮኖሚ ችግር እን
ድትወጣ በምትጥሩበት በአሁኑ ጊዜ በመተባበርና በመረዳዳት ፈንታ የእስልምና ሃይማ
ኖት ተከታዮች የሆኑት ሰዎች ምናልባት የጐደለባቸው ነገር ቢኖር በሰላማዊ መንገድ
አስተዳደሩን መጠየቅና በተገቢው ጊዜ መልሱን ማግኘት ሲችሉ አላግባብ ያቀረቡዋ
ቸው ጥያቄዎች የኢትዮጵያንሕዝበክርስቲያን የሚያሳዝኑና መሠረተ እምነቱን የሚነኩ
ሆነው ተገኝተዋል ።

ከቀረቡትም ጥያቄዎች ጥቂቶቹ፡-

፩ኛ / ኢትዮጵያ የክርስትና ደሴት አይደለችም ፤
፪ኛ / መንግሥቱ ከሃይማኖት የተለየ ይሁን፤
፫ኛ / የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥቱ ከተደገፈች
የእስልምና ሃይማኖትም በመንግሥቱ ይደገፍ ፤

፬ኛ / የእስልምና ሃይማኖት ሚስዮን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ይፈቀድለት
፭ኛ / የሞራልና የግብረ ገብነት ትምህርት በየትምህርት ቤቱ እንዳይሰጥ የሚሉ ይገ
ኙባቸዋል ።

ሀ / ኢትዮጵያ ሀገራችን ቀደም ሲል በሕገ ኦሪት ፤ በኋላም በሕገ ወንጌል ፤ አምና
የክርስቲያኖች ደሴት በመባል በታሪክ የታወቀች ስለሆነች ይኸው በማያዳግም ሁኔታ
በይፋ እንዲረጋገጥላት ።



www.ethiopianorthodox.org

ለ / ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አቋምም ሆነ አመራሩ በተቀደሰ የክር ስትና ትምህርት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ፤ ይህ አቋም የማይለወጥ መሆኑ እንዲረጋገጥለት ።

ሐ / የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ቀርቶ ገና በመካና በመዲና ሳይ መሠረት በአብርሃና በአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ማለት ከ፫፻፴ ዓመተ ምህረት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መሠረታዊት ቤተ ክርስቲያን መሆኗንና በመንግሥቱም የተደገፈች ሁና ከመኖሯም በላይ የተለመደውን የክርስትና ተግባሯን በመፈጸም በችግር ጊዜ የተሰደዱትን የእስልምና ሃይማኖት ተቀብላ በሰብአዊ ርኅራኄማስተናገዷ ሲታወቅ፤ ይኸን ጥንታዊ ታሪክ ለማቃወስ የሕዝበ ክርስቲያንን ስሜት ለመንካት የተሞከረ የፈጠራ ወሬ ስለሆነ ፤ ይህ ለህዝቡ መቶ ዓመታት የቆየው ታሪካዊና ሕገ መንግሥታዊ አቋሟ የማይቃወስ መሆኑ እንዲረጋገጥላት ።

መ / በማንኛውም ክፍለ ዓለም ካንድ በላይ የመንግሥት መደበኛ ሃይማኖት አለመኖሩ ሲታወቅና በኢትዮጵያም በአንድ አገር ፤ በአንድ ዘወድ ፤ በአንድ መንግሥት ፤ ሁለት መደበኛ ሃይማኖት ማቋቋም የማይቻል መሆኑን እያወቁ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸው በመንግሥት የተደገፈ እንዲሆን መጠየቃቸው አገባብ የሌለው መሆኑ እንዲገለጥለት ።

ሠ / የእስልምና ሃይማኖት ሚሲዮን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ መጠየቅ በእስልምና ሃይማኖት ምክንያት በ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሀገራችን ላይየደረሰውን ከባድ ችግር መልሶ ለማምጣት የታቀደ ስለሆነ ፤ መንግሥቱ ይህን ተገንዝቦ ሊሆን የማይገባ መሆኑን ለሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲገለጥለት ።

ረ / የሞራልና የግብረ ገብነት ትምህርት በየትምህርት ቤቱ አይሰጥ ብሎ መጠየቅ የኢትዮጵያ ሕፃናት በመልካም አስተዳደግ እንዳያድጉና ጥሩ ዜጐች እንዳይሆኑ የተወጠነ ተንኮል መሆኑ ታውቆ ትምህርቱ የማያቋርጥ መሆኑ ለሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲገለጥለት እየጠየቅን ፤

የሕዝበ ክርስቲያኑንም መንፈስ በፍጹም የሚያረካ መግለጫ በተገቢው ባይሰጥ ግን አባቶቻችን ከጠላት ጋር በመታገል አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውን አፍሰው ያቆዩንን የተወዳጅ ሀገራችንን ነፃነት ለመንካት ፤ የሕዝቡንም አንድነት ለመለያየት የታሪካችንና የጥንታዊ ቅርሳችንን ጠባቂ የእምነታችንን ምንጭ የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንም ሕገ መንግሥታዊ አቋም የተሰነዘረባትን ከእውነት የራቀ ወሬ ለማስተባበል የኢዮትጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በአንድነት ተባብሮ አስፈላጊውን ርምጃ ለመውሰድ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን እያሳሰብን ፤ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያናችን አዲስ በሚሻሻለው ሕገ መንግሥት ሰፋ ያለ መብትና ጠንከር ያለ አቋም እንዲኖራት ብርቱ ጥረት እንደሚደረግበት የማይታበል መተማመኛ በተቻለ ፍጥነት እንዲሰጠው የሚጠባበቅ መሆኑን ይገልጻል ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝበ ክርስቲያን

ክቡር ጠ/ሚኒስትር ልጅ እንዳልካቸው መኰንን የተወካዮቹን ምእመናንአቤቱታ ከአዳመጡ በኋላ በቅርብ ጊዜ ውሳኔ እንደሚሰጥበት ገልጸው ምእመናኑንበትእግሥት እንዲጠባበቁ አደራ በማለት አሰናብተዋቸዋል ።

ሙሉጌታ ወ/ ሚካኤል



www.ethiopianorthodox.org